# በኢትዮጵያ የፌደራል መንግሥታዊ ሥርዓት አወቃቀር ላይ የሚነሡ ጥያቄዎች

በገብሩ አሥራት /ዓረና/

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ በጣም ጥንታዊ የሆነ ታሪክ ካላቸውና ከሰሐራ በታች ከሚገኙ የአፍሪቃ አገሮች አንዷ ስትሆን እስከ ሦስት ሺሕ ዓመታት የሚሄድ ታሪክ ያላት አገር ናት፡፡ በደጋማው አቢሲንያ የመጀመሪያው ንግሥና የተመሠረተው በአንደኛ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ሲሆን መንግሥትነት የተመሠረተውም በአክሱም ነበር፡፡ (Loves Aelen 2002: 4) ኢትዮጵያ ባለ ረዥምና በጣም ጥንታዊ የሆነ ሥልጣኔ ባለቤት ብትሆንም አሁን የያዘችውን ጂኦግራፍያዊ ቅርጽ የያዘችው ግን በአገሪቱ የነበሩ የአካባቢ መሪዎችና ነገሥታት ዘንድ የሠለጠነና የተማከለ መንግሥት የመመስረት ፍላጐት እየጠነከረ ከመጣ በኋላ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ገደማ ነበር፡፡

በሰሜናዊ የአቢስንያ ግዛት ማእከላዊ መንግሥት ያለመመሥረቱ ለረዥም ጊዜ የተፈጠረው ዘመነ መሣፍንት ተብሎ የሚታወቀው ምስቅልቅል ተከትሎ ኋላ ላይ አጼ ቴዎድሮስ ተብለው የአገሪቱ ንጉሥ የሆኑት ከሳ ሃይሉ በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ኢትዮጵያን ዘመናዊና በአንድ ማእከላዊ መንግሥት የምትመራ የማድረግ እቅድ በመያዝ ተንቀሳቀሱ፡፡ (ባህሩ ዘውዴ 2002፡ 11)

ይሁን እንጂ ይህን እቅዳቸውን ተግባር ላይ እንዳያውሉ ከመሣፍንቱና መኳንንቱ በተለይ ደግሞ እስከዛሁ እለት ድረስ በኢትዮጵያ የንግሥና ሂደት ትልቅ ሚና ከነበረው ከኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በኩል ጠንካራ ተቃውሞ ደርሶባቸው ነበር፡፡ ይህ ብርቱ ተቃውሞ በናፒር የተመራው የእንግሊዝ ወረራ ታክሎበት የአጼ ቴዎድሮስን የንግሥና ዘመንና ኢትዮጵያን የተዋሃደችና የሠለጠነች የማድረግ ህልማቸው እንዲቋረጥ አደረገው፡፡

የአጼ ቴዎድሮስ ማእከላዊ መንግሥት የመመሥረት ሙከራ በ1868 ዓ.ም ከወደቀ በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥትነትና ማእከላዊ ሥልጣን ይገባናል የሚሉ የየአከባቢው ተቀናቃኝ መሪዎች በብዛት ብቅ አሉ፡፡ ከተቀናቃኞቹ መካከልም የትግራዩ ካሳ ምራጭ (አጼ ዮሃንስ)፣ የሸዋው ሚኒልክና የጐጃሙ ተክለሃይማኖት ይገኙበታል፡፡ በመጨረሻም አጼ ዮሃንስ፣ የየአካባቢው ነገሥታት በየአካባቢያቸው ያላቸውን የማስተዳደር ሥልጣን እውቅና በመስጠት የንጉሠ ነገሥትነት ሥልጣናቸውን አረጋግጠው ለ17 ዓመት ያህል ገዙ፡፡

አጼ ዮሃንስ ከሸዋው ንጉሥ ሚኒልክ ጋር ያደረጉት ስምምነት በሃገሪቱ ታሪክ ላይ ልዩ ሚና ስለነበረው እዚህ ላይ ማንሣቱ ተገቢ ነው፡፡ አጼ ሚኒሊክ ከንጉሠ ነገሥት ዮሃንስ ጋር ስምምነት ከማድረጋቸው በፊት የዮሃንስን ትእዛዝ በተከታታይ ያለመቀበል ሁኔታ ያሳዩ ነበር፡፡ ይህ የአጼ

ሚኒሊክ ሁኔታ ያናደዳቸው አጼ ዮሃንስ ሚኒልክን ለመዋጋት ኃይላቸውን አሰባስበው ወደ ሸዋ ተንቀሳቀሱ፡፡ ይህን ጦርነት ሊያስከትል የሚችለውን ጥፋት የተገነዘቡት ሚኒሊክ በሁለቱ መኻል እርቅ እንዲወርድ ጠይቀው በሰሜን ሸዋ ድንባሮ በሚባል ቦታ የሠላም ስምምነት ተደርጐ ቡለቱ መኻል ያንዣበበው ጦርነቱ እንዲቆም ተደረገ፡፡ በዚህ ስምምነት መሠረት አጼ ዮሃንስ የሚኒልክን የሸዋ ንጉሥነትንና ወደ ደቡብ የሚያደርጉትን የማስፋፋት እንቅስቀሴ ሕጋዊነትን ይፋዊ እውቅና ሰጡ፡፡ ዶ/ር ዘውዱ ውብ እንግዳ የፌደራሊዝም ታሪክ በኢትዮጵያ በሚለው ጽሑፋቸው እንዳስቀመጡት «ስምምነቱ አጼ ሚኒልክ በደቡብ፣ በምዕራብና በምሥራቅ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ለማስመለስ የሚያደርጉት ጥረት አጼ ዮሃንስ እውቅና መስጠት እንዳለባቸው አካትቶ ነበር» (ውብ እንግዳ 2005፡ 179) ሚኒልክም በተመሳሳይ የአጼ ዮሃንስን የማይገሰስ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነትንና ለሳቸው የመገበርን ጉዳይ ተቀብለዋል»፡፡

ከዚህ በኋላ የአጼ ሚኒልክ ዋነኛው ተግባር ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴና መስፋፋት መቀጠል ሆነ፡፡ በዚህ ሂደት የተለያዩ በየአካባቢው የነበሩ የብዙ ብሄረሰቦችና ጐሳዎች ግዛቶችና ገዢዎችን በመቆጣጠርና በማንበርከክ ሰፊ ድል አስመዘገቡ፡፡ «በኢትዮጵያ የማእከላይ መንግሥት የመመሥረት ጉዳይ ዳግማዊ ሚኒሊክ ሥልጣን እስኪይዙ ድረስ (እኤአ 1889 - 1913 ዓ/ም) አልተነሣም ነበር ፡፡ ሚኒልክ ግዛታቸውን ከመካከለኛው የደጋው አካባቢ ወደ ደቡብና ምሥራቅ የኢትዮጵያ አካባቢ በማስፋፋት የአሁኑን ዳር ድንበር የያዘች ከ80 በላይ ብሄር ብሄረሰቦችን ያቀፈች ኢትዮጵያ መሠረቱ፡፡ በጣም ጠንካራ ባህላዊ ንግሥናዎች፣ አንድ አንዶቹ ከዛ በፊት በደጋው ግዛት ሥር ያልነበሩ እንደነ ኦሮሚያ፣ ወላይታ፣ ሲዳማ፣ ጉራጌ፣ ከፋ ወዘተ በማሸነፍ በቁጥጥር ስር አስገቡ፡፡ (Loves Aelen 2002: 5)

በዚህ ሂደት የመስፋፋት ዘመቻ ከተከሄደባቸው ህዝቦች በጣም ጠንካራና ደማዊ ተቃውሞ ያጋጠመ ቢሆንም የተሸነፉት ንጉሦችና መሪዎች በመጨረሻ የሚኒልክ አገልጋዮች እንዲሆኑ ወይ ደግሞ በሌሎች የሰሜን ተወላጅ ባለሥልጣኖች እንዲተኩ የተደርጉበት ሁኔታ ነበር፡፡

አጼ ዮሃንስ የድርቡሽን ወረራ በመከላከል ጦርነት በ1981 ዓ.ም በምዕራብ የአገሪቱ ክፍል በሞቱ ጊዜ ሚኒልክ የኢትዮጵያ መሪ ሆኑ፡፡ የአጼ ሚኒልክ የሥልጣን ዘመን በአውሮፓ መሪዎች መካከል አፍሪካን የባዕድ ግዛት ለማድረግ ትልቅ ውድድር የታየበት ጊዜ ነበር፡፡ ይህ በቅኝ ገዢዎች የታየው አፍሪካን ከፋፍሎ የመቆጣጠር እንቅስቃሴ በአጼ ሚኒልክ ላይ የኢትዮጵያን ሉአላዊ ግዛቶች አሳልፎ እስከ መስጠት ያስገደደ ትልቅ ጫና ፈጥሮ ነበር፡፡ በጣልያኖች፣ እንግሊዞችና ፈረንሳዮች መካከል በአፍሪካ ቀንድ የቅኝ ግዛት የማስፋፋት ወድድሩ ሲጠናክር ሚኒልክ ከቅኝ ገዢዎቹ ጋር ስምምነት በመፈራረም ግጭትን ለማስወገድ ሞክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ የቅኝ ገዢዎችን እንቅስቃሴ በዚህ መንገድ ሊገቱት ስላልቻሉ ወደ ጦርነት መግባት የግድ ሆኖባቸው በ1988 ዓ.ም ከጣልያኖች ጋር ባደረጉት ጦርነት በአድዋ ጣልያኖችን አሸንፈዋል፡፡ (ባህሩ ዘውዴ 2002፡ 77)

ከአድዋ ጦርነት ድል በኋላ በሰሜን በኩል ከመረብ ጀምሮ በደቡብ በኩል እስከ ቦረና ድረስ ጥያቄ ውስጥ የማይገባ የሚኒልክ ግዛት መሆናቸው ተረጋገጠ፡፡ የአጼ ሚኒልክ ከባዕድ ገዢዎች ጋር መገናኘት ኢትዮጵያን ዘመናዊ የማድረግ ራእያቸው አጠናክሮ መንግሥትን ለመምራት በተነጻጻሪ ዘመናዊ የሚባል ቢሮክራሲ ለመመሥረትና ዘመናዊ ትምህርትና ዘመናዊ የመገናኛ ሥርዓት እንዲያስፋፉ ገፋፍቷቸዋል፡፡ ይህ ሆኖም ግን የሚኒልክ አገዛዝ በዋነኝነት በዘውዳዊ ሕጐችና ድንጋጌዎች የሚመራ እንጂ ሕገ መንግሥት ያልነበረው በመሆኑ ጊዜ ያለፈበት ፈላጭ ቆራጭ ሥርዓት ሆኖ የቀጠለ ነበር፡፡

አጼ ሚኒልክ ከሞቱ በኋላ ሥልጣኑን ለመቆጣጠር ይፈልጉ በነበሩ የተለያዩ ተቀናቃኞች መካከል ጠንካራ ፉክክር ታየ፡፡ በመጨረሻም ከተፎካካሪዎች አንዱ የነበሩት ራሥ ተፈሪ ሌሎች ለንግሥናው የበለጠ ሕጋዊነት ወይም ቅርበት የነበራቸው ወራሾች በማሸነፍ ሥልጣኑን በመቆጣጠር ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ በመባል ነግሠዋል፡፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ ንግሥና ከመረጋገጡ ጋር በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ከሆነው ሕገ-መንግሥት ጋር አዲስ ዓይነት የአገዛዝ ሥርዓት መስፋፋት ጀመረ፡፡ ይህ ሕገ-መንግሥት የህዝቦችን መሠረታዊ መብቶች የጠቃቀሰ ቢሆንም ዋነኛ ዓላማው ወይም ፍላጐቱ ግን የንጉሡን ፍፁማዊ ሥልጣን ለማረጋገጥ ወይንም ሕጋዊ ለማድረግ ነበር፡፡

የአጼ ኃይለ ሥላሴ የረዥም ዓመታት ንግሥና በ1967 ዓ.ም የወታደራዊው ደርግ ወደ ሥልጣን ከመምጣት ጋር ተሳስሮ ለውድቀት ተዳረገ፡፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ ሕገ-መንግሥት በደርግ መንግሥት ሥራ ላይ እንዳይውል ታገደ፡፡ ደርግ የተለያዩ አዋጆችን በማውጣት አገሪቱን ለ12 ዓመት መግዛቱን ቀጠለ፡፡ ወደኋላ ገደማ የራሱን የአንድ ፓርቲ አገዛዝና የግዛቱን ማእከላዊነት የሚያረጋግጥ፡ የህዝቦች መሠረታዊ መብቶችና የዴሞክራሲ ጥያቄዎችን ለይስሙላ የነካካ ሕገ-መግሥት አፀደቀ፡፡ ይህ የደርግ ሕገ-መንግሥት የደርግን ሥርዓት ለመጣል በጥንካሬ ይታገሉ የነበሩ ተቃዋሚዎችን ሊያሰባስብ ወይም ሊያቀራርብ አልቻለም፡፡ ይልቁኑ በደርግ አገዛዝ ዘመን ኢትዮጵያ፡ በሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢ የተለያዩ የብሄር ብሄረሰቦች ድርጅቶች በመመሥረት (የኦሮሞ ነፃነት ግንባር፣ ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ፣ የአዓፋር ነፃ አውጪ ድርጅት፣ የምዕራብ ሶማልያ ነፃ አውጪ ግንባር፣ የጋምቤላ ህዝቦች አርነት እንቅስቃሴ፣ የቤንሻንጉል እንቅስቀሴ ወዘተ.) የትጥቅ ትግል የሚካሄድባት አገር ስለነበረች ትልቅ ቀውስ ውስጥ የገባችበት ጊዜ ነበር፡፡ እንደነ የኤርትራ ነፃ አውጪ ድርጅትና ህዝባዊ ግምባር አርነት ኤርትራ የመሳሰሉ ድርጅቶችም ኤርትራን ነጻ ለማውጣት ይታገሉ ነበር፡፡ እንደነ የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ፣ መላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄና የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረት የመሳሰሉት ኅብረ ብሄራዊ ድርጅቶችም የትጥቅ ትግልና በትጥቅ ትግል ማዕቀፍ የማይካተቱ የተለያዩ ትግሎች ያካሄዱ ነበር፡፡ እነዚህ ኅብረ ብሄራዊ ድርጅቶች ማእከላዊነት መሠረት ያደረገ የመንግሥት ሥርዓት ለማቋቋም የታገሉ የነበሩ ቢሆኑም፡ በብሄር ደረጃ የተደራጁ ድርጅቶች ያራምዱት የነበረውን ደርግን የመጣል ዓላማ ይጋሩ የነበሩ ናቸው፡፡ አለመታደል ሆነና እነዚህ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አብረው የሚሰባሰቡበት አነስተኛ (Minimum) የጋራ የመግባቢያ ሠነድ ወይንም የመታገያ ፕሮግራም

ሊያዳብሩና ተጋግዘው ሊሠሩ ግን አልቻሉም፡፡ እንዳውም ግልፅ ባልሆነ ርእዮተ ዓለማዊና ፖለቲካዊ ፉክክር ውስጥ ገብተው እርስ በእርስ ይፋጁ ነበር፡፡

ደርግ ካልታጠቁና ከታጠቁ የፖለቲካ ቡድኖች በይበልጥ ደግሞ ከህዝቡ በገጠመው ተቃውሞ ሥልጣኑን ለማስጠበቅ ስላልቻለ ለውድቀት ተዳረገ፡፡ ይህ ውድቀት በብሄር ብሄረሰብ ደረጃ የተደራጁ እንደነ ኢህአዴግና ኦ ኤል ኤፍ ተሰባስበው መንግሥት እንዲፈጥሩ  በር ከፈተ፡፡ የደርግ ውድቀትን ተከትሎ የተፈጠረው የሽግግር መንግሥት የኢህአዴግ ህወሓት የበላይነት የነበረው ቢሆንም አጀማመሩ ላይ ሰፋ ያለ መሠረት እንደነበረው ግን አይካድም፡፡ የሽግግር መንግሥቱ የኦሮሞ ነጻ አውጪ ግንባርን አካትቶ ነበር፡፡ ይህ ግንባር አዲሶቹ «የአቢስንያ ገዢዎች» የሚላቸውን ይቃወም የነበረ ቢሆንም በሚኒስትሮች ካቢኔ ተወክሎና 12 የምክር ቤት መቀመጫዎችን ይዞ የሽግግር መንግሥቱን ተቀላቅሎ ነበር፡፡ በሽግግር መንግሥቱ እንደነ ኢህአፓና መኤሶን የመሳሰሉ ዋነኞቹ ኅብረ ብሄራዊ ፓርቲዎች  ያልተካተቱ ቢሆኑም ብዙ ብሄራዊና ብሄረሰባዊ ድርጅቶችና ጥቂት አገራዊ ፓርቲዎችም በሥልጣን ክፍፍሉ ሥርዓት ተካትተው በዛን ጊዜ በተካሄደው የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ቻርተርን ባፀደቀው ኮንፈረንስ ተሳትፈዋል፡፡

የሽግግሩ ቻርተር ከሁሉም በላይ የብሄር ብሄረሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል ለሚለው መብት እውቅና የሰጠ ሠነድ ነበር፡፡ በአንድ ማዕከላይ መንግሥት ትመራ ለቆየችው ኢትዮጵያ ይህ ፍፁም የተለየ አዲስ ክስተት ነበር፡፡ በዚህ በኩል የመጣው ለውጥ የኢትዮጵያ መንግሥት አወቃቀር ለወደፊቱ ምን እንደሚመስል አመላካች ነበር፡፡ የሁለት ዓመት ተኩል የሽግግር ዘመኑ ካለፈ በኋላ ኢትዮጵያ በሽግግሩ ግዜ በፀደቀው ቻርተር መሠረታዊ እምነቶች ላይ የተመሠረተ ሕገ-መንግሥት አፀደቀች፡፡ ጠንካራ ሊባሉ የሚችሉ እንደነ የኦሮሞ ነጻ አውጪ ግምባርና ኢህአፓ የመሳሰሉ ብሄራዊና አገራዊ ፓርቲዎች በሕገ-መንግሥቱ የማርቀቅና የማፅደቅ ሂደት አልተሳተፉም ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በርካታ አገራዊና ብሔራዊ ፓርቲዎች በሂደቱ ተሳትፈዋል፡፡ ያም ሆኖ ግን ኢህአዴግ ዋነኛው ጠንካራ ተዋናይ ስለነበር የድርጅቱ የፖለቲካ ፕሮግራም ይዘቶች በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ ተካትተው እንዲጻድቁ አድርጓል፡፡

ሕገ-መንግሥቱ ከውልደቱ ጀምሮ በተለያዩ ፖለቲካዊ ቡድኖችና ሙሁራን ሂስ እንደቀረበበት ነው፡፡ በብሄር ብሄረሰቦች ላይ የተመሠረተ ፌደራሊዝም ለኢትዮጵያ አይጠቅምም፣ የብሄር ብሄረሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት ትክክል አይደለም፤ የሚሉ በሕገ-መንግሥቱ ላይ የሚቀርቡ ዋነኞቹ ሁለት ሂሶች ናቸው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ሕገ-መንግሥቱ በፌደራሊዝም መረህ ወይንም ጽንሰ ሐሳብ ላይ የተመሠረተ ስለመሆኑም ጥያቄ ይነሣበታል፡፡ የሕገ-መንግሥቱ ተግባራዊነትና የዴሞክራሲ ሂደቱ በአጠቃላይ በተለያዩ አካላት ይተቻል፡፡ የተወሰኑት በዴሞክራሲያዊ ሂደቱ የሚታዩ ጉድለቶች አሉ ሲሉ ሌሎች ደግሞ ሂደቱ በአጠቃላይ ኢ-ዴሞክራሲያዊና አምባገነናዊ ነው ይላሉ፡፡ እንደነዚህ ዓይነቶቹ ሂሶች ጠንከር ባለ መንገድ የሚቀርቡ ቢሆንም የሥርዓቱ ደጋፊዎች ግን የፌደራል ሥርዓቱ ትክክለኛነትና የዴሞክራሲ ሂደቱ ጥንካሬ ከማስተጋባት ወደኋላ አላሉም፡፡

በዚህ ፅሑፍ መጀመሪያ በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የተከተቱትን በብሄር ላይ
የተመሠረተ ፌደራሊዝምንና የመገንጠል መብትን በሚመለከት የሚነሡትን አንድ አንድ

የሐሳብ ልዮነቶች ወይንም አከራካሪ ነጥቦች ለመዳሰስ እሞክራለሁ:: በመቀጠል አሁን በኢትዮጵያ ባለው የፌደራል ሥርዓት ውስጥ አሉ የምላቸውን ጉድለቶች ለምሳሌ ከበጀት ክፍፍል ገር የተሳሰረ ፋይናነሳዊ ፌደራሊዝም፡ ብሄሮች ወይንም ክልሎች በማእከላይ መንግሥት ያላቸው ውክልና፡ ፍትሐዊ የሥልጣን ክፍፍልና፡ ሕገ-መንግሥት ፍርድ ቤት ያለ መኖር ጉዳይ፡ የገዢው ፓርቲ (ኢህአዴግ) በክልሎች ጉዳይ ያለው ጠንከራ ጣልቃ ገብነት ወዘተ. ያጠቃለሉ ጉዳዮችን እዳስሳለሁ::

## 2. ብሄር ብሄረሰብን መሠረት ባደረገ ፌደራሊዝምና በመገንጠል መብት ዙርያ የሚነሡ አካራካሪ ጉዳዮች

### 2.1 ብሄር ብሄረሰብን መሠረት ባደረገ ፌደራሊዝም ዙርያ የሚነሡ ክርክሮች

በብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሠረተ የፌደራል ሥርዓት በሀገሪቱ ሕገ-መንግሥት በ1987 ዓ.ም ከፀደቀ ወዲህ በጉዳዩ ደጋፊዎችና ተቃዋሚዎች መከከል ሰፊ ክርክር እየተደረገ ይገኛል:: ይሁን እንጂ የሚሰነዘሩት ክርክሮች በጠንካራ ንድፈ ሐሳባዊና ፅንሰ ሓሳባዊ ምርምር ላይ የተመሠረቱ ሳይሆን በአብዛኛው ከግላዊ ስሜትና በጥናት ካልተደገፉ ስጋቶች የሚነሱ ናቸው:: በአሁኑ ግዜ በጉዳዩ ጥናትና ምርምር ላይ የተመሠረቱ ትንተናዎች በተሻለ ሁኔታ የሚገኙ በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚደረጉ የድጋፍና የተቃውሞ ክርክሮች እየበሰሉና መልክ እየያዙ መጥተዋል:: በኢትዮጵያ በብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሠረተ ፌደራሊዝምን የሚቃወሙ ተመራማሪዎች ይህ ዓይነቱ የአወቃቀር ሥርዓት የግለሰብ መብት የማይገሰስ እንዲሆን ያደረገውን ዓለማዊዉ የሊቨራል ዴሞክራሲን መነሻ ሐሳብ የሚጻረር ነው ይላሉ:: ግለሰቦች በቡድንና በስብስብ መታጨቅ የለባቸውም፤ የቡድን ወይንም የወል መብት የማንኛውም ዓይነት ነጻነት መሠረት የሆነውን የግለሰብ መብት ጠላትና አደናቃፊ ነው ይላሉ:: የዚህ ሐሳብ አራማጅ «መሳይ ከበደ» (2006) እንዲህ በማለት ይከራከራሉ:: «የሊቨራል ሞዴል የግለሰብ መብት የሚያምን ሲሆን፣ የሌኒንስቶች ፎርሙላ ደግሞ የጋራ ወይንም የቡድን መብት ከግለሰብ መብት በላይ አድርጐ ይዉስዳል:: ስለሆነም ጎሰኝነት የሥልጣን የበላይነት የማግኘት ፍላጐታቸው በሊቨራል መንገድ ማሳካት ያልቻሉ፡ ተሰሚነትና ተቀባይነት ያጡ ምሁራን ፍጡር ነው:: ስለዚህም የቡዱን መብት አራማጆች /ጎሰኞች/ ሊቨራሊዝምን ለመቃወም በመጀመሪያ ማርክስ ሌኒንነትን የተቀበሉ፣ ከዛም ሌሎች የሚወዳደርዋቸውን ምሁራን በማግለል የራሳቸው ተፈጥሯዊና ግላዊ መብት በሌሎች

ላይ በመጫን የተጨቆኑ ቡድኖች መብት ለመወከል የተነሱ ናቸው» ይላሉ፡፡ ከላይ የተገለጸውን ሐሳብ በመጻረር የኢትዮጵያ የፌደራል ሥርዓትን የሚደግፉት ደግሞ መብትን የግለሰብ የቡድን በማለት ከፋፍሎ ማየት ትክክል አይደለም፤ የግለሰብና የቡድን መብቶች እርስ በራሳቸው የሚጻረሩ አይደሉም ይላሉ፡፡ በአሁኑ ዘመን የሊበራል ዴሞክራሲ ንድፈ ሐሳብ ሳይቀር ለቡድን መብቶችና (ለምሳሌ የሴቶች መብት፣ የአናሳ ህዝቦች መብት) የብሄረሰቦች በራሳቸው ቋንቋ የመጠቀም መብት፣ የራሳቸውን ባህል የማራመድ መብት እውቅና ሰጥቷል ይላሉ፡፡ ስለዚህ መሳይ ከሌኒንስት ንድፈ-ሐሳብ ጋር ያስተሳሰሩት ለቡድን መብት እውቅና የመስጠት ጉዳይ በሊበራል ፖለቲካዊ አስተሳሰብም ተቀባይነት ያገኘ ጉዳይ ነው ይላሉ፡፡

በብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሠረተ ፌደራሊዝምን የሚደግፉ «ጊዶዮን ከሆን» (2006) የሚቀጥለውን ይላሉ «በብሄር ብሄረሰብ ወይንም ክልል ላይ የተመሠረተ ፌደራሊዝም የተለያዩ የህዝቡ ቡድኖች ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚወከሉበት የተሻለ መዋቅር የሚሰጥ ነው፡፡ የራስን ቋንቋ የመጠቀም መብት የብሄሮች የማንነታቸው መገለጫ ነው ለሚለው ንድፈ ሐሳብ እምብርት ነው፡፡» (ጊዶዮን 2006፡ 189)

ሌላ የዚሁ ሐሳብ ደጋፊ "Will Kymlicka" (2006) የሚቀጥለውን ይላሉ፡፡ «በብዙ ብሄረሰቦች ላይ በተመሠረተ የፌደራሊዝም ሥርዓት የኑኡሳን ብሄረሰዎችን ብሄራዊነት ማስተናገድ ለህዝቦች መሠረታዊ መብቶችና ፍላጐቶች የሚፈጥረው አደጋ የለም፡፡ በተጻራሪ የኑኡሳን ብሄረሰዎችን ብሄራዊነት ለማጥፋት ወይንም ለመጫን የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ሙከራ ሊበራል ዴሞክራሲያዊ መብቶችን የሚገድብ ሲሆን ምናልባትም ብሄርተኞችን ከሰላማዊ እንቅስቃሴ ወደ አፍራሽ (ሰላማዊ ያልሆነ) ግጭት የሚገፋ ይሆናል፡፡» (Kymlicka 2006: 45)

«ከሚሊካ» በብሄሮች ላይ የተመሠረተ ፌደራሊዝም በህዝቦች መሠረታዊ መብቶች ላይ የሚያመጣው አደጋ የለም የሚል አቋም ቢያራምድም፡ በአፍሪካና በኢትዮጵያ የጉዳዩ ተግባራዊ አፈጻጸም በሚመለከት ግን ጨለምተኛ አገላለፅ አለው፡፡ ቱርቶን (2006) የከሚሊችን አቋም ባጭሩ ሲገልጹ «በኢትዮጵያና በአፍሪካ ያለው በብዙ ብሄሮች ላይ የተመሠረተ ፌደራሊዝም በሚመለከት ከሚሊካ የደረሰበት ድምዳሜ ብሩህ ተስፋንና ጨለምተኝነትን ያዘለ ነው፡፡ በኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ናይጀርያ ውስጥ ያለው የብሄር ልዩነትን በተሳካ መልኩ ለማስተናገድ ከተጠቀሰው ፌደራሊዝም ውጭ ሌላ አማራጭ ፎርሙላ የማያይ በመሆኑ ብሩህ ገጽታው የሚገለጽበት ሲሆን፣ ጨለምተኛ የሚያረገው ደግሞ ምዕራቡ ዓለም ብዙ ብሄሮች ላይ የተመሠረተ ፌደራሊዝም በሰላማዊ መንገድ

ተግባር ላይ እንዲውል ያደረጉ ሁለት ሁኔታዎች ማለትም የብሄሮች ብሄረሰቦች ግንኘነት የግጭት ምንጭ መሆኑ ማብቃቱና በምዕራቡ ዓለም በሰፊው የሚታይ በሊበራል ዴሞክራቲክ እምነቶች ላይ የተፈጠረው ሰፊ የህዝቡ ድጋፍ ወይንም መግባባት በአጠቃላይ በአፍሪከ የሌሉ መሆናቸው ነው»:: (David Turtor 2006: 5) ከሚሊካ ራሱ በኢትዮጵያ በብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሠረተ ፌደራሊዝም አፈጻጸም በሚመለከት ያለው ስጋት እንደሚከተለው ይገልፃል:: «ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ አንዳንድ አናሳ ቡድኖች የራሳቸውን አባላት የሰብአዊ መብት አደጋ ላይ የሚጥል ሊበራል ያልሆነ ሃይማኖታዊና ባህላዊ እምነት ሊኖራቸው ይችላል:: ለምሳሌ በኢትዮጵያ ሁኔታ የኢትዮጵያ የፌደራል አውቶኖሚ ተጠቃሚ የሆኑት ብዙ አናሳ ቡድኖች ውስጥ እየታዩ ያሉት ሊበራል ያልሆኑ ተለምዷዊ ወይንም ባህላዊ ሕጎች ተግባራዊ የሚሆኑ መሆናቸው አሳሳቢ ነው» (Will Kymlicka 2006: 51)

በብሄር ላይ የተመሠረተ ፌደራሊዝም ደጋፊዎችና ተቃዋሚዎች የፌደራሊዝም አወቃቀር ወይንም አመሠራረት በሚመለከትም ይለያያሉ:: በብሄር ላይ የተመሠረተ ፌደራሊዝምን የሚቃወሙ ወገኖች በብሄር ብሄረሰቦች ላይ የተመሠረቱ ፌደራሊዝም መመሥረት ለመበታተን መንገድ መክፈት ነው፣ ምክንያቱም የራሳቸው አውቶኖሚ እና መንግሥት ከተሰጣቸው የብሄር ብሄረሰቡ ቡድኖች በራሳቸው ጠባብ አካባቢያዊ ፍላጐቶች ተውጠው የሰፋውን የጋራ ፌደራላዊ የመንግሥት ፍላጐቶች ወይንም ጥቅሞች በመርሳት ለመገንጠልና ለብሄራዊ መበታተን አደጋ ተጋላጭ ሊሆኑ ይችላሉ ይላሉ:: ብዙዎች የዚህ ሐሳብ አራማጆች የአሁኑ የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ችግሮች ከዚህ አወቃቀር ጋር የተሳሰረ እንደሆነ አድርገው ያቀርቡታል::

በተጻራሪ የኢትዮጵያ ፌደራል አወቃቀር ደጋፊዎች የብዙ ብሄርና ብሄረሰቦች በሆኑት እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች የብሄር ብሄረሰቦችን ህላዌና ጥያቄ ግምት ሳያስገባ መራመድ ምናልባት የተሳሳተ ጊዜያዊ የአንድነትን ስሜት ፈጥሮ በመጨረሻ ግን በኃይል አንድ ላይ እንዲሆኑ የተደረጉትን አናሳ ህዝቦች በፍላጐት ላይ ያልተመሠረተውን አንድነት በመቃወም በእርግጠኘነት የቀጣይ ቀውስ፣ መገንጠል፣ መበታተንና መከፋፈል መነሻ የሚሆን ነው::

በብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሠረተ ፌደራሊዝምን መከተል አለመከተል በሚመለከት የሚራመዱ ደጋፊና ተቃዋሚ ሐሳቦች ቢኖሩም በአሁኑ ጊዜ በብሄር ብሄረሰቦች ላይ የተመሠረተ ፌደራል ሥርዓት በዓለማችን እየተለመደ እንደመጣ ግምት ውስጥ ማስገባት ጠቃሚ ይሆናል:: እንደነ ሲዊዘርላንድ፣ ካናዳ፣ ቤልጂየም የመሳሰሉ የምዕራብ

አገሮች በብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሠረተ የፌደራል ሥርዓት እየተከተሉ ነው፡፡ ከደቡቡ የዓለማችን ክፍልም ህንድና ናይጀርያ ተመሳሳይ መንገድ ተከትለዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ወይም አመለካከት፣ በብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሠረተ ፌደራሊዝም በአንዳንድ አገሮች በውጤታማነት ተግባር ላይ ስለዋለ እንደ ኢትዮጵያ ላሉት የብዙ ብሄር ብሄረሰብ አገሮች የሚያስኬድ ሥርዓት ሊሆን ይችላል፡፡ እንዳውም አሁን ባለው ሁኔታ መከባበር፡ ለማንነት እና ለልዩነት እውቅና መስጠትና የብሄር ብሄረሰቦችን ሥልጣን ማጐልበት (empower ማድረግ) ለጠንካራ አገራዊ አንድነት መሠረት ሊሆን የሚችል ነው፡፡

**2.2 በመገንጠል መብት ዙርያ የሚነሡ ክርክሮች**

ኢትዮጵያ በብሄር ብሄረሰቦች ላይ የተመሠረተ ፌደራሊዝምን በመከተልዋ ምክንያት የተነሣ ያለው ተቃውሞ ይበልጥ እየተባባሰና እየከረረ የመጣው «በኢትዮጵያ የሚገኙ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የመገንጠልን መብትን ያካተተ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ያልተገደበ መብት አላቸው» የሚለውን ድንጋጌ በሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ 39 ተከትቶ ከጸደቀ በኋላ ነው፡፡ (የፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት 1995፡ 96) አንዳንድ ሐያስያን ይህንን አንቀፅ በሕገ-መንግስቱ መካተቱ አገሪቱን ለመበታተን መንገድ የሚከፍት አደገኛ እርምጃ አርገው ያዩታል፡፡ በመሆኑም ተግባሩን የኢትዮጵያ ጠላቶችና በታኞች ተግባር አድርገው ያዩታል፡፡ መገንጠል መብት ተደርጎ በግልፅ እውቅና መሰጠቱ ጠባብ ብሄርተኞችን በማበረታታት በአንዲት ኢትዮጵያ አብረው ሊኖሩ ይችሉ የነበሩትን ወገኖች እንዲገነጠሉ ይገፋፋቸዋል፡፡ ስለሆነም ይህ እንዳይሆንና የኢትዮጵያን አንድነት እንዲጠበቅ አንቀፅ 39 ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲ ሰረዝና ከሕገ-መንግስቱ ወጥቶ እንዲጣል ይጠይቃሉ፡፡ «መገንጠል» እንደ ሐሳብ ከሶሻሊስትዋ ሶቭየት ኅብረት የተኮረጀ ነው፡፡ በሶቭየት ኅብረት ተሞክሮ ለመበታተን መነሻ የሆነ ስለሆነ ይህንን አደገኛ ሙከራ በኢትዮጵያ መደገም የለበትም ይላሉ፡፡

የዚህ ዓይነቱ አመለካከት አራማጅ የሆኑት ዶ/ር ውብእንግዳ በሚከተለው መልክ ይከራከራሉ «ፌደራሊዝምን የሚከተሉ አገሮች የመገንጠልን መብት በሕገ-መንግስታቸው አላካተቱም፡፡ ፌደራሊዝምና ፌደራል ሥርዓትን የሚመሠረቱ አካላት በስምምነት ለመኖር የሚያደርጉት ስምምነት ውጤት ስለሆነ እንዲገነጠሉ የሚገፋፋቸው ቅድመ ሁኔታ ወይም ሁኔታ ሊኖር አይችልም፡፡ የመገንጠል ጥያቄ ከተነሣ የፌደራል ሥርዓቱን እድገትና ፌደራሊዝሙን በመሠረቱት አባላት መካከል ሊኖር የሚገባውን ትብብር የሚያደናቅፍ ይሆናል፡፡ (ውብ እንግዳ 2005፡ 264)»

ሌሎች ፀሐፊዎችም በረዥም ሂደት የፌዴሬሽኑን አንድነት ሊያናጋ ይችላል በሚል የመገንጠል መብትን በኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት መካተቱ ይቃወማሉ ብቻ ሳይሆን ስጋታቸውም ይገልፃሉ፡፡ ሎቨስ አለን በሚከተለው መንገድ ይከራከራሉ፡-

«በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሞዴል ላይ ያለው የተለመደ ትችት የመገንጠልን መብት ያካተተ መሆኑ ነው። (Brietzke 1995, Abbenk 1997, Matti 1995, Paul 2005, Cohen 1994) ከላይ የተገለፁት ትችቶች በፌደራሊዝም አቀንቃኞች የመገንጠል መብት የፌደራል ሥርዓትን አደጋ ላይ ይጥላል በሚሉ በእንደነ Duchack (1987) ይደገፋል።» እኔ ግን እንደገና የኪንግስን (King's) የፌደሬሽንን ትርጉም መነሻ በማድረግ «የመገንጠልን መብት የኢትዮጵያን ሥርዓት ፌደራላዊ ከመሆን ውጭ አያደርገውም በሚል መከራከር እመርጣለሁ። የኢትዮጵያን ሕገ-መንግስት በማንበብ የመገንጠል መብትን በፖለቲካና በአሰራር (Procedure) ተግባር ላይ ማዋሉ ከባድ እንደሆነ በግልፅ ማየት ይቻላል። በማንኛውም መነሻ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል አይመስልም። ይሁን እንጂ ሂስ አቅራቢዎቹ በትክክል እንዳመለከቱት ይህንን መብት በሕገ-መንግሥቱ መካተቱ ቡድኖችንና ሪጅኖችን ይህን አማራጭ ወደ መሞከር የሚገፋፋና ብሎም በረዥም ሂደት የፌደራል ሥርዓቱን ያናጋ ይሆናል» (Lovise Aalen 2002: 62)

የመገንጠል መብት ተቃዋሚዎቹ ሌሎች መሰረታዊ መብቶች ባልተረጋገጡበት አገር የመገንጠልን መብት በሕገ-መንግሥቱ እንዲካተት ማድረግ ትርጉም ያለው አይደለም ወይም ህዝቡን ማታለል ነው ወይንም ግብዝነት ነው በሚልም ይከራከራሉ። በጉዳዩ ላይ የአለን (Aelen) አመለካከት እደሚከተለው ነው። «በኢትዮጵያ ፌደራል ሥርዓት አወቃቀር በብዙ ጸሐፊዎች ያልተስተዋለ ግልፅ የሆነ ተቃርኖ አለ። (Abblnk 1997, Paul 2000, Brietzke 1995) በአንድ በኩል የአገሪቱ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የተወሰነ ሁኔታዎች ካልተሟሉላቸው ከፌደሬሽኑ የመውጣት መብት ተሰጥቷቸዋል። ይህ በኢትዮጵያ ፌደሬሽኑን የመሠረቱት አካላት ያላቸው ነጻነት በሌላ ፌደራል ሥርዓት ከሚገኙት አካላት ካላቸው ነጻነት የበለጠ ያደርገዋል። ይሁን እንጂ በሌላ መንገድ ሲታይ ደግሞ ፌደሬሽኑን የመሠረቱት አባላት ያላቸው ሥልጣን በተነጻጻሪ በጣም ኣናሳ ነው። የክልል መንግሥታት የፌደራል ሥርዓቱ ጥገኞች ናቸው። በBrietzke አገላለጽ ጥቂት የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መፍትሄዎች ያስቀመጠው ሕገ መንግሥት የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መገለጫ በሆነው የመገንጠል መብትና በመጠኑ በተቀመጠው የባህላዊ ነጻነት መብት መካከል ያለውን ክፍተት ለመፍታት የሚቻልበትን አግባብ በሚገባ አላስቀመጠም።»

የመገንጠል መብት ደጋፊዎች ከዚህ በተለየና በተጻራሪ መልኩ ይከራከራሉ። ሁሉም ሕገ-መንግሥቶች አንድ ዓይነት እንዳልሆኑ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የተወሰኑ ብሄር ብሄረሰቦች በሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች ልፅልና ሲጨቆኑ በቆዩበት አገር የመገንጠል መብትን በሕገ-መንግሥቱ መካተቱ የነዚህ የተጨቆኑ ብሄር ብሄረሰቦች መብት እንዲከበር እንደዋስትና የሚያገለግልና ዴሞክራሲያ ጥልቀት እንዲኖረው የሚያደርግ ነው ይላሉ። የዚህ ሐሳብ ደጋፊዎች መገንጠልን በሰላማዊ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የፈቀዱ ሃገራትን እንደ ምሳሌ ይጠቅሳሉ።

የዚህ መብት ዋነኛ ተዋናይና መሃንዲስ የሆነው በሥልጣን ላይ ያለው የኢህአዴግ መንግሥት ይህንን መብት በማስተጋባት በዋነኛነት ይጠቀሳል። ቀደም ያሉ የኢህአዴግ ጽሑፎች የዚህ መብት

ትክክለኛነት ለማስረገጥ ይሞክሩ የነበረው የሶቭየት ኅብረትን አብነት በመጥቀስ ነበር፡፡ የአሁኖቹ የኢህአዴግ ዶክመንቶች ወይንም ጽሑፎቹ ደግሞ የቺኮሶላቫክያና የካናዳ ምሳሌዎችን ይጠቅሳሉ::

«የህዝቦች መብት የመገንጠል መብትን ይጨምራል የምንልበት አንዱ መሠረታዊ ምክንያት መሠረታዊ የዴሞክራሲ መርህ ስለሆነና፣ ማንኛውም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረታዊ የዴሞክራሲያዊ መብቶችን ሳያፍን ይህንኑ መብት ሊረግጥ ስለማይችል ነው:: ይህንኑ መሠረታዊ ሐቅ ለመገንዘብ ሁለት የመገንጠል መብትን በህገ መንግሥተቸው ያሰፈሩ ነገር ግን ዴሞክራሲያዊ የሆኑ አገሮች ልምድ እንውሰድ፡፡ በአንድ ወቅት ቼክና ስሎቫኪያ በአንድ ምንግሥት ሥር የሚተዳደሩ ሁለት ህዝቦች ነበሩ:: በአገሪቱ ዴሞክራሲ በሰፈነበት ወቅት በሁለቱ ህዝቦች መካከል የነበረው የሻከረ ግንኙነት በኃይል ሳይሆን በሠላማዊ መንገድ መፈታት አማራጭ የሌለው ሆኖ ተገኘ፡፡ ...ስለሆነም ዴሞክራሲን ጠብቆ ለማቆየት ሪፈረንደም አካሂዶ የህዝቡን ውሳኔ ከመቃበል ሌላ አማራጭ ስላልነበረ በዚህ ሂዴት ቼኮችና ስሎቫኮች ተነጣጥለው የየራሳቸው መንግሥታት ያቋቋሙበት ሁኔታ ሊፈጠር ቻለ፡፡በካናዳ ኩዊቤክ በሚባለው ፈረንሳይኛ ተናጋሪ በሚኖርበት አካባቢና በሌላው እንግሊዝኛ ተናጋሪ አካባቢ የቆየ ቅራኔ እንዳለ ይተወቃል፡፡ ፈረንሳይኛ ተናጋሪዎች ውስጥ ከሌላው ካናዳዊ ተነጥለን የራሳችንን መንግሥት ማቋቋም አለብን የሚል ሰፋ ያለ ስሜት በመኖሩ ካንዴም ሁለቴ የሪፈረንደም ጥያቄ ተነስቷል፡፡ የካናዳ ሕገ መንግሥት ዴሞክራሲያዊ ቢሆንም በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች ምክንያት የመገንጠል መብትን ያካተተ አልነበረም፡፡ ይሁንና የመገንጠል ጥያቄ በህዝቡ ውስጥ በተነሣበት ሁኔታ ይህንኑ ለማፈን መሞከር ዞሮ ዞሮ ጠገንጠልን የሚያስቀር መሆኑ እጅግ አጠራጣሪ ከመሆኑ ባሻገር የዴሞክራሲ ሥርዓት ወደ ማክሰም እንደሚያመራ ለካናዳውያን ግልጽ ነበር፡፡ የዴሞክራሲ ሥርዓታቸውን ጠብቆ ለማቆየት የነበራቸው ብቸኛ አማራጭ ሪፈረንደምን መፍቀድና የመገንጠል ጥያቄውን በዴሞክራሲያዊ አኳኋን መታገል ነው፡፡» (ልማት፣ ዴሞከራሲና አብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ ኢህአዴግ 2006: 104-6)

ኢህአዴግ የመገንጠል መብትን እንደ አንድ መሠረታዊ የዴሞክራሲ መብት እውቅና እስከተሰጠው ድረስ ጥያቄው ሲነሣ በዴሞክራሲ መንገድ ስለሚስተናገድ በሕገ-መንግሥት ውስጥ መካተቱና አለመካተቱ የሚፈጥረው ልዩነት ትንሽ ነው በማለት ኢህአዴግ እየተከራከረ ይገኛል::

ሌሎች ተመራማሪዎችም የመገንጠልን መሠረታዊ መንስኤዎች ጠለቅ ብለው ለመፈተሽና ለማየት ሞክረዋል:: «ከላይ እንደተገለፀው መዋቅራዊ እወቅና ያጣና መድልዎ እየደረሰብኝ ነው ብሎ የሚያምን ቡድን ልክ የመገንጠል መብቱን በሕግ እንደተረጋገጠለት ቡድን ሁሉ የመገንጠል አቀንቃኝ ሊሆን ይችላል» (Adeney 2000: 18) :: አደናይ የራስዋን አመለካከት እንዲህ በማለት ታጠናክራለች: «ብሄር ብሄረሰብና ክፍለ ሃገራዊ አከላለል ከተገጣጠሙ የብሄር ብሄረሰብ ግጭትን ያባብሳል፣ መገንጠልን የበለጠ እውን ያደርጋል ብሎ መከራከር የመገንጠል ፍላጎት መኖሩን ግምት ውስጥ ያስገባል:: ይህም ፌደራሊዝምን እንደ አንድ የብሄሮችና ብሄረሰቦችን ግጭቶች ማለዘቢያ ዘዴ ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል መርሳት ነው:: በኅብረ ብሄራዊው ሥርዓት ወይንም መንግሥት የብሄር ብሄረሰቦች ደህንነት የተጠበቀ ከሆነ የመገንጠል ፍላጐት ወይንም መንሥኤ ይሳሳል:: በተጨማሪም የብሄር ብሄረሰዎች ደህንነት እስከ ተጠናከረ ድረስ ብሄራዊ ተቋሞቹ ራሳቸው ተአማኒነትን ሊያጠናክሩ ይችላሉ:: (Adeney 2000: 7)»

የቀድሞዋ ሶቭየት ኅብረት የብሄር ብሄረሰቦች እስከ መገንጠል የሚለውን መብት ተግባራዊ በማድረግ ወይንም በመከተል ፈር ቀዳጅ ልትሆን ትችላለች፡፡ ይሁን እንጂ የዚህ መብት እውቅና ቦልሸቢኮች ያራምዱት ከነበረው ርእዮተ ዓለማዊ መስመር የመነጨ አልነበረም፡፡ ይልቁኑ ከነበሩት ተጨባጭ ችግሮች በመነሣት ያኔ የነበረውን ጨቋኝ መንግሥት ለመጣል የተጠቀሙበት ስልታዊ መፈክር ነበር፡፡ ምንም እንኳ ኋላ ላይ የርእዮተ ዓለሙ አካል እየሆነ ቢመጣም መገንጠል የላብ አደሩ ዓለም አቀፋዊነትን ይሰብኩ በነበሩ ቦልሸቢኮች የሚስተጋባ ዋነኛ መፈክር አልነበረም፡፡ ጉዳዩ ሲነሣበት የነበረው ግምት ለመገንጠል መብት እውቅና መስጠት መገንጠልን ሳይሆን አንድነትን ያጠናክራል የሚል ነበር፡፡ ይህ ኢህአዴግም ቀደም ሲል ሲያራምደው የቆየ የክርክር አቅጣጫ ነበር፡፡ እዚህ ላይ ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ይህንን ዓይነት ትንታኔ ወይንም እምነት እውን መሆን የሚችለው ዴሞክራሲ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ሲሆንና ግለሰቦች፡ ዜጐችና ብሄር ብሄረሰቦች ዴሞክራሲውን በተሟላ መንገድ ሲጠቀሙበት ነው፡፡ የሶቭየት ኅብረት ተሞክሮ እንደሚያሳየን ዴሞክራቲክ ሥርዓት በሌለበትና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ባልተረጋገጡበት ሁኔታ የመገንጠል መብትን እንደ መርህ መከተል ውጤቱ መበታተን ሊሆን ይችላል፡፡ ሶቭየት ኅብረትን የመሠረቱት አካላት ዴሞክራሲን በአግባቡ አላጣጣሙም፡ ስለሆነም የኮሚኒስት ፓርቲው የቁጥጥር ዓቅሙ ሲላላ የፌደሬሽኑን አባላት ራሳቸውን ከኮሚኒስት ፓርቲው ጨቋኝ አገዛዝ ለማውጣት ከፍ ያለ ፍላጐት አሳዩ፡፡ ከዚህ የተነሣም የሶቭየት ፌደራላዊ ሥርዓት ቅጽበታዊ መፈራረስ አጋጠመው፡፡

«በሶቭየት ኅብረት እንደተደረገው ሁሉ የኢትዮጵያ ገዢ ፓርቲም በፓርቲውና ተያያዥነት ባላቸው መዋቅሮች አማካይነት በክልል መንግሥታቱ ጠንካራ ክንድ አለው፡፡» (አሰፋ ፍሥሃ 2006: 156) አሰፋ ፍስሃ በኢተዮጵያ ያለውን የፓርቲና የመንግሥት ግንኙነቶች እንደሚከተለው ይገልጸዋል፡፡ «አጠቃላይ አመለካከቱ ይህ ነው፡፡ አንድ ፓርቲ በፌደራልና በክልል ያሉትን መንግሥታት ከተቆጣጠረና የተማከለ የፓርቲ መዋቅር ካለው የክልል መንግሥታትን ሥልጣን መዳከሙና የክልሎች ነጻነት (Autonomy) መዳከሙ የማይቀር ነው፡፡» በመቀጠልም እንዲህ ይላል «በኢትዮጵያ የፓርቲው መዋቅር የፌደራል የሥልጣን ክፍፍሉን ያዳክማል፣ ክልላዊ መንግሥታትን የፌደራል መንግሥት ጥገኞች ያደርጋል» ይላል፡፡ አሰፋ ፍሥሃ 2006: 157፡፡ ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይ አስተያየት ያለው ሌላው ምሁርም የሚቀጥለውን ይላል፡፡

«በኢትዮጵያ በሙከራ ሂደት ላይ ባለው ፌደራሊዝም ብዛት ያላቸው ከላይ ወደ ታች የሚወርዱ አመራሮችና አስተዳዳሪዎች ይሰተዋላሉ፡፡ በባጀት ዝውውር ወይንም ክፍፍል በፌደራል መንግሥት ላይ ካለው ጥገኝነት በተጨማሪ የክልል መንግሥታት ለፌደራል መንግሥቱ ሰፊ ቁጥጥር የተጋለጡ ናቸው፡፡ በሕግ ሁሉም የክልል መንግሥታት ስፋት ያለው ሥልጣንና ሐላፊነት ተሰጥቷቸዋል፡፡ የፌደራሉ መንግሥት ጣልቃ ገብነት ሳይኖር አብዛኛውን የክልላቸው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች በነፃነት

ማስተዳደር ይጠበቅባቸዋል:: ይሁን እንጂ በተግባር፣ የአገሪቱ የፌደራል ሥርዓትን የማስተዳደር ተሞክሮ አናሳ በመሆኑና በክልሎቹ መከከል የአስተዳደርና የአመራር ብቃት ልዩነት በመኖሩ ምክንያት በክልሎቹ ጉዳይ ላይ የማእከላዊ መንግሥት ጣልቃ ገብነት ቀጣይ እንዲሆን አድርጓታል:: (አየነው 2002: 138-139):: በአጠቃላይ ፌደራል ሥርዓቱን የመሠረቱት አካላት ላይ ያለው የፓርቲው ጠንካራ ጣልቃ ገብነትና የክልሎችን ሥልጣን የመጋፋቱ ጉዳይ በኢትዮጵያ ባሉትን ብሄር ብሄረሰቦች መካከል ነጻ ግንኙነት እንዳይኖር በመገደብ ለመበታተን ወሳኝ ምክንያት ሊሆን ይችላል::

በኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት የመገንጠል መብት ቢካተትም ጉዳዩ ገና መቋጫ ያገኘ አይመስልም:: በተወሰኑት የአገራችን ክልሎች ያሉ ሊህቃን አሁንም የነጻነት ጥያቄ በማንገብ እስከ ትጥቅ ትግል የሚደርስ እንቅስቀሴ እያካሄዱ ይገኛሉ:: ሕገ መንግሥቱ በጸደቀበት ያልተካተቱትና ከዛ በኋላ የተቋቋሙ በርካታ ፓርቲዎችም ይህን አንቀጽ እንደማይቀበሉ አበከረው ይገልጻሉ:: በኢህአዴግ ተቀባይነት ያላገኘ ቢሆንም፣ የመገንጠል ጥያቄ በኢትዮጵያ አንዱ አንገብጋቢና አወዛጋቢ ጉዳይ መሆኑ መታወቅ አለበት:: በአሁኑ ጊዜ የመገንጠል ጥያቅ በማንሣት ትጥቅ አንግበው የሚዋጉና በሕገ-መንግስቱ የተካተተው አንቀፅ 39 መብታቸው የሚያስጠብቁበት ዋስትና አድርገው የሚወስዱ ብሄር/ብሄረሰቦች የመኖራቸው ያህል ይህ አንቀጽ እንዲለወጥ የሚንቀሳቀሱ በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶችም እንዳሉ መደበቅ አይቻልም::

የመገንጠል መብት ትልቁ ችግር በተሳሳተ መንገድ የሚቀርብ ጉዳይ መሆኑ ነው:: «መገንጠልን የሚሹ ኃይሎች» የመገንጠልን መብት ዴሞክራሲያዊ ይዘትና ያሉበትን ተጨባጭ ሁኔታ ሳያገናዝቡ እንደ መጨረሻ ግብ ይወስዱታል:: መሠረታዊ ሰብአዊ መብቶችና ነጻነቶች ሳይከበሩ የመገንጠል መብትን ለብቻው ለይቶ ማስተጋባት ለሊህቃኖቹ ይሁን ከነሱ ጋር ለተሳሰሩ የብሄር ብሄረሰቦች ህዝቦችና ለኢትዮጵያ ህዝብ በአጠቃላይ የሚያገለግል ወይንም የሚጠቅም አይደለም:: በሌላ መንገድ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ከሌሎች የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የዴሞክራሲ ጥያቄዎች ነጥሎ ማየት ወይንም ለጥያቄዎቹ ግምት ሳይሰጡ ማለፍና ማዳፈን፣ የመገንጠልን ፍላጎት የሚያጠናክር ይሆናል:: በአገራችን እየተያዩ ያሉ ጽንፎች እነዚህ ናቸው:: በመሆኑም የመገንጠል ጥያቄ በአግባቡ ስላልተያዘ የተፎካካሪ ኃይሎች መቀራረብና መደጋገፍ ሳይሆን መካረርና መለያየት እያስከተለ ነው::

## 3. አሁን ባለው የፌደራል ሥርዓት ዙርያ የሚነሡ ችግሮች

### 3.1 ክልሎች በፌደራል ሥርዓቱ ያላቸው ውክልናና ቁጥጥር ደካማ መሆኑ

የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት እንዲሁ ሲታይ ክልሎችን በሁሉም መንግሥታዊ ተቋማት ማለትም በፓርላማ፣ በሕግ-ተርጉሚና በሕግ-ፈፃሚ አካል ወዘተ. የተደገፈ የራሳቸው መንግሥትና ሕገ-መንግሥት እንዲኖራቸው ይፈቅዳል:: ከፍ ብሎ እንደተገለጸው የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት በጣም ስሱ ለሆነው የብሄር

ብሄረሰቦች የመገንጠልን መብት እንኳ እውቅና ይሰጣል። ይህም ሆኖ ግን እነዚህ በክልሎች ይተገበራሉ ተብለው የሚገመቱት ይፋዊ ሕገ-መንግስታዊ መብቶች ፌደራል ሥርዓቱን የመሠረቱት ክልላዊ አካላት በፌደራል ደረጃ ጉልህ ወይም ትርጉም ያለው ሚና እንዲኖራቸው አላደረገም።

ኢትዮጵያ የፌደራል የተወካዮች ም/ቤት ማለትም የአገሪቱን ጥቅም በሃገር ደረጃ የሚያስጠብቅና ዜጎች የሚሣተፉበት የታችኛው ፓርላማና ፈደራል ሥርዓቱን የመሠረቱት አከላት ጥቅም የሚያስከብረው የፌደሬሽን ም/ቤት ያካተተ ሁለትዮሽ (Bicameral) የፓርላማ ሥርዓት የምትከተል አገር ብትሆንም የፌደሬሽን ምክር ቤቱ ሥልጣን ግን እጅግ የተገደበ ነው። ኤለን እንደምትለው «የፌደሬሽን ምክር ቤት በፌደራል ፓርላማው ውስጥ የሚካሄደውን ተራ ሕግን የማፅደቅ ሂደት እንኳ የመቆጣጠር ምንም ሚና የለውም። ይህ ደግሞ ከሌሎች ፌደራላዊና ሁለትዮሽ ፓርላማ ሥርዓቶች አሠራር ጋር ይጋጫል። ከላይ እንደተገለጸው የፌደሬሽን ምክር ቤቱ ጣልቃ መግባትና ውሳኔ መስጠት የሚችለው የሕገ-መንግሥት ጉዳዮችና የፌደራልና የክልል ግንኙነቶች ጥያቄ ውስጥ ሲገቡ ብቻ ነው ። ይህ ደግሞ በፖሊሲዎች ላይ በሚደረግ ክርክርና የፌደራል ሕግን በማመንጨት ሂደት ክልሎች በፌደሬሽን ም/ቤቱ በኩል ምንም ዓይነት ተሳትፎ ወይንም ድምጽ እንደሌላቸው ያመለክታል። የኢትዮጵያ የፌደራሊዝም አወቃቀር በሌሎች የፌደረሽኑ መዋቅሮች፣ በፌደራል ም/ቤቱና በፌደረሽን ም/ቤት በጣም ዝቅተኛ ቁጥጥርና ክትትል ለሚደረግለት ለአስፈፃሚው አካል ሰፊ የማንቀሳቀሻ ቦታ ይሰጣል። በአብዛኞቹ ፌደራላዊ ሥርዓቶች ነጻ የሆነ የሕገ-መንግሥት ፍርድ ቤት ሕገ-መንግሥቱን በመተርጐምና የሚለወጥበትን ሁኔታ በማመቻቸት ወሳኝ ሚና አላቸው»። (ሎቢስ አለን 2002:60-61)

ስለሆነም በኢትዮጵያ ፌደራል ሥርዓት የሚታየው ትልቁ ጉድለት ቀዋሚ ያልሆነው የፌደሬሽን ም/ቤት በተለይ ከተወካዮች ም/ቤት ጋር ሲነጻጸር ጠንካራ ሥልጣን የሌለው መሆኑ ነው። የፌደሬሽን ም/ቤት ሕግን ለማመንጨትና ለማፅደቅ አይችልም። ይህ ሥልጣን ለሥራ አሰፈጻሚውና ለተወካዮች ም/ቤት ብቻ የተሰጠ ነው። የክልሎች የባጀት ክፍፍል ቀመር በማውጣትና በክልሎች መካከል የሚነሣ ግጭትን በማየት ብቻ የተወሰነ አካል ነው። ፍሰሃ እንደሚገልፀው «ኢትዮጵያ ሕግ የሚያጸድቅ ሁለተኛ ቻምበር የላትም። ክልሎቹ ቀደም ብሎ እንደተመለከተው በፌደራሉ መንግሥት በሚተገበሩት ወይንም በሚፀድቁት ሕጐች ላይ ምንም ዓይነት ቁጥጥር የላቸውም» (አሰፋ ፍሥሃ 2006: 152) የፌደሬሽን ም/ቤት ምንም የአስፈጻሚ ሥልጣን የሌለውን የአገሪቱን ፕሬዝደንት የመምረጥ የጋራ ሥልጣን ቢኖረውም የሌሎች የፌደራል ባለስልጣናት ማለትም በጣም አስፈላጊ ናቸው የሚባሉት ሚኒስትሪዎችንና መ/ቤቶችን የሚመሩ ባለሥልጣናት የመምረጥ ሥልጣን ግን ተነፍጓታል። ከነዚህ ሁሉ አንጻር ሲታይ የፌደሬሽን ምክር ቤት ፌደሬሽኑን የመሠረቱትን አካላት ዋነኞቹ ፍላጐቶች ይወክላል ሊባል አይችልም።

### 3.2 ስምምነት ላይ የተመሠረተ የሥልጣን ክፍፍል ያለመኖሩ

የኢትዮጵያ ፌደራሊዝም አንዱ ድክመት የፌደራሊዝም ዋነኛ መነሻ ወይንም ምንጭ የሆነውን ፌደራሊዝሙን በመሠረቱት መካከል ሊኖር የሚገባውን የሥልጣን ክፍፍል የሳተ መሆኑ ነው። ኢህአዴግ ፌደራሊዝሙን ለመሠረቱት አከላት ሥልጣን ለማከፋፈል የካቢኔውንና የሠራዊቱ ተዋፅኦ ለማስተካከል መሞከሩ የሚታወስ ነው። እንዳውም ከፍተኛ ያለመጣጠን ፈጥሯል የተባለውንና እጅግ ጠንካራ ይባል የነበረውን የህወሐት ሠራዊት  እስከ መበተን የሄደ እርምጃ በመውሰድ የሥልጣን ሚዛኑን ለማስተካከል ሞክሯል። ይህ እርምጃ ግን ከሥልጣን ክፍፍል አንፃር ብዙ ትርጉም አልነበረውም። በሥልጣን ክፍፍል መርህ ላይ ያልተመሠረተና  ሌሎችን የፌደራሉ የሥልጣን ተጋሪዎች ያላሳተፈ ሆኖ በሥልጣን ላይ ባለው ፓርቲ ብቻ የተፈጸመ ጉዳይ ነበር።

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሥርዓት ግጭቶችና አለመግባባቶችን ለማስቀረት ወይንም ለማስወገድ ከቻሉት ካለፉት ሌሎች የሥልጣን ክፍፍል ተሞክሮዎች የተማረ አይመስልም። ሩቲሚ ሲበሩ የናይጀርያውን ተሞክሮ በመጥቀስ እንዲህ ይላል። «በጣም ጠቃሚው ጉዳይ የፌደራሊዝም ፅንሰ ሐሳብ መደበኛ ባልሆነ ግን ደግሞ በስፋትና በአዲስ ፈጠራ «ዞኒንግ» ወይም «ሮቴቲንግ» በሚል አጠቃላይ የሥልጣን ክፍፍል መርህ እንደገና መዋቀሩ ነው። ዞኒንግ የሚለው መርህ የናጀርያ በርካታ መንግሥታትና ብሄር ብሄረ ሰቦችን እንደገና በማሰባሰብ ለሥልጣን ክፍፍልና ዝውውር በሚያመች አነስተኛ በሆኑ ጂኦፖለቲካዊ አካባቢዎች መዋቀሩ ነው። እነዚህ  አካባቢዎች በፌደሬሽኑ ውስጥ ያሉትን የአካባቢን፣ የባህልንና የብሄር ፖለቲካን ልዩነቶች መሠረት ያደረጉ ናቸው። ሮትሚ ሱቤሩ፡ 2006፡ 76»

የምርጫና የሕገ-መንግሥታዊ የሥልጣን ክፍፍል ሥርዓት አስፈላጊነት በተመለከተ አደናይ  በሚቀጥለው መንገድ አጽንኦት በመስጠት ያቀርበዋል። «ቅርጹና አመሰራረቱ ቢለያይም ፌደራሊዝም በአብዛኛው ጊዜ የሁለትዮሽ ወይንም ባይካሜራል ሕግ አውጪ አከል ያስፈልገዋል። ሁለትዮሽ ሕግ አውጪ አከል መኖሩ እንደ አንድ የፈደራል ሥርዓቱ መሥራቾችን ጥቅምና ፍላጎት ማስጠበቅያ ዘዴ የፌደራል ሥርዓቶች የተለመደ መገለጫ ነው። ይሁን እንጂ የክልሎች ሥልጣን ወይንም ፍላጐቶች የሚረጋግጡበት ሌሎች አግባቦች/ዘዴዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ ሁለትዮሽ ህግ አውጪ ግዴታዊ ባህሪያዊ መገለጫ ነው ማለት አይደለም። ለምሳሌ በምርጫ ሥርዓት ወይንም በሃገር ደረጃ በሚደረግ ሕገ-መንግሥታዊ የሥልጣን ክፍፍሎች (አደነይ 200: 1)»

ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር መራራ ጉዲና የሥልጣን ክፍፍልን አስፈላጊነት በሚመለከት አጽንኦት በማድረግ እንደሚከተለው ይከራከራሉ፡፡ «አሁን ካለው የፖለቲካ ቀውስ ለመውጣት ሁለት ጉዳዮች ወሳኞች ናቸው፡፡ የገዢው ፓርቲ ሥልጣን በብቸኝነትና በበላይነት የመያዝ ፍላጐትና ድምር ውጤቱ ዜሮ የሆነ የፖለቲካ ጨዋታ ማቆም እንዲሁም በአንዳንድ ሊሂቃን የሚጠየቀው ትርፍ የሌለው(ቅጥያጣ) የመገንጠል ጥያቄ መተው ነው፡፡» ምረራ ጉዴና - 2006: 129

የሥልጣን ክፍፍል ሥርዓት የፌደራሊዝም አስፈላጊ ህዋሳት ወይንም መሰረቶች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ እውን መሆን የሚችሉት ሙሉ ተጠያቂነትና ግልፅነትን የሚሰጥ፡ ዜጎችና ክልላዊ መንግሥታት ነጻ ሆነው የሚወያዩበት ሂስ የሚያቀርቡበት ሰፊ ምህዋር ባለበት ሁኔታ ነው፡፡ አሁንም አደናይ የዴሞክራሲያዊ ፌደራሊዝም አስፈላጊነትን አጽንኦት ሰጥቶ ሲገልጽ እንደሚቀጥለው ይላል፡፡ «በመጨረሻ "Watts" ገና እስከ አሁን ድረስ የእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ፌደሬሽን አብነት የለም. . .ይህ ደግሞ የተሟላ ዴሞክራሲያዊ ሂደት ለውጤታማ ፌደሬሽን ቅድመ ሁኔታ መሆኑ ያመለክታል፡፡ (1999: 9)፡፡ ይህ እውነት ሊሆን ይችላል፡ ነገር ግን በዘር ላይ የተመሠረተ ግጭት ለመፍታት የሚንቀሳቀሱትን፡ ፌደራሊዝም እውነተኛ ላልሆኑ ዴሞክራሲዎችም እንደ አንድ የመፍቲሄ አቅጣጫ ከመውሰድ ሊያግዳቸው አይገባም፡፡ (አደነይ 200: 25-26)

### 3.3 ሕገ-መንግሥታዊ ፍርድ ቤት ያለመኖር

በፌደራል ሥርዓቶች ቀጥተኛና ጎናዊ የሆኑ የሥልጣን የቁጥጥርና ሚዛን ማስጠበቅያ ሥርዓት አለ፡፡ ጐናዊ ቁጥጥሩ በአብዛኛው ለ3ቱ የመንግሥት አካላት ማለትም ለሕግ አውጪው፣ ሕግ አስፈፃሚውና ሕግ ተርጓሚው ወይንም የዳኝነት ሥርዓቱ፡ ቀጥተኛው ደግሞ ፌደራልንና የክልል አካላትን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በነዚህ በተጠቀሱት አካላት መካከል ልዩነት ወይንም ግጭትና ክርክር ከተፈጠረ በመሠረተ ሐሳብ ደረጃ፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥ ከፖለቲካ ነፃ የሆነና ገለልተኛ አካል መኖር አለበት፡፡ ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ሁኔታ በክልልና በፌደራል የፖለቲካዊ አካላት መካከል የሚፈጠሩ ችግሮች ለመፍታት የፌደሬሽን ም/ቤቱ የህገ መንግሥት አጣሪ ም/ቤት ያቋቁምና ችግሮቹ አጣርቶ የጥናቱ ውጤት ከውሳኔ ሐሳብ ጋር አስተሳስሮ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለፌደሬሽን ም/ቤት መልሶ ያቀርባል፡፡ ሰብሩ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሥርዓት የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ትክክለኛ እንዳልሆነ በሚቀጥለው መንገድ ይገልጸዋል፡፡ «በሌላ መንገድ ኢትዮጵያ ሕገ-መንግስታዊ ልዩነቶች ወይንም

ግጭቶች ሲፈጠሩ የማስታረቁ: ማጣራቱና ውሳኔ የመስጠቱ ሥራ ነጻ ለሆነ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሳይሆን ለፖለቲካዊ አካል፣ ማለትም የፌደራል ሥርዓቱ ሁለተኛ ክፍል ወይንም ቻምበር ለሆነው ለፌደሬሽን ም/ቤትና የፈደረሽን ም/ቤቱ አካል ለሆነው ሕገ-መንግሥት አጣሪ ኮሚቴ መስጠትዋ በሌሎች ያልተለመደ ነው» (ሱብሩ 2006: 88)

በኢትዮጵያው ፌደራላዊ ሥርዓት ያለው ክፍተት የፌደሬሽን ም/ቤቱ የፌደራል ሥርዓቱ መስራቾችን ለመወክልና ጥቅሞቻቸውን ለማስጠበቅ የቆመ ነው ቢባልም ሕግ አውጪ ሆኖ ሊሠራ የማይችል መሆኑ ነው:: የፌደረሽን ም/ቤት የፌደራል አከላትን የሚወክል አካል ነው ተብሎ ቢገመትም በአብዛኛው የፖለቲካ ፓርቲ አባላትን ያቀፈና ወገናዊ የሆነ አካል ነው:: ከዚህ ሌላ የተወካዮች ም/ቤቱና የፌደራል ም/ቤቱ አባላት የሚያጠቃልለው የሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ኮሚቴ አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ከተቀበላቸው በኋላ የሚመሠረት አከል ነው:: ሕገ-መንግሥታዊ ጉዳዮችን የሚያጣራ ነጻ የሆነ ፍርድ ቤት ላለማቋቋም ያሚቀርበው ምክንያት መነሻው ግልጽ አይደለም:: ግልጸ የሆነው ነገር ግን፡ በጣም በትልቁ የገዢው ፓርቲና የፓርቲ አካላት ጫና ያለው የሕገ-መንግሥት አጣሪ ም/ቤት፡ በማንኛውም ዓለም አቀፋዊ መመዘኛ ብቃት የሌለው መሆኑ ነው::

### 3.4 በክልላዊ ጉዳዮች የገዢው ፓርቲ ከባድ ጣልቃ ገብነት መኖሩ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሥርዓት ላይ ያለው ሌላው ሂስ የገዢው ፓርቲ በክልላዊ ጉዳዮች ውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ላይ ጠንካራ ጫናና ጣልቃ ገብነት የሚመለከት ነው:: ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ በክልላዊ ተቋማት፡ በክልላዊ ምክር ቤቶችና የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት ጭምር፡ የነዚህ አካላት ተጠሪነት ለመረጣቸው ሕዝብ ሳይሆን ለፓርቲው እስኪመስል ድረስ በጣም ጠንካራ ጣልቃ ገብነት አለው:: እውነቱን ለመናገር በአንድ አንድ ሁኔታ የፓርቲው አባላት ወይንም ደጋፊዎች የክልል መንግሥታት ብቸኛ ተወካዬች ናቸው:: ይህን በሚመለከት አለን Rikerን (1964) በመጥቀስ «. . .የፓርቲው የአደረጃጀት ሥርዓት የፌደራል ሥርዓቱ የሥልጣን ክፍፍል ሊያዳክም ወይንም ሊያጠናክር ይችላል:: አንድ ፓርቲ የፌደራሉና የክልሉ ወይንም የክልሉ መንግሥት ከተቆጣጠረና የተማከለ የፓርቲ መዋቅር ካለው የክልል መንግሥታትን ሥልጣን በዛውም የክልሎን የራስ ገዝ መብት (Autonomy) ሊያዳክም

ይችላል። የፓርቲ ሥርዓት በቅንነት እንዲከፋፈል፡ እስከታች ድረስ እንዲወርድ ከተደረገ ወይንም ደግሞ የክልል መንግሥታት ከገዢው ፓርቲ ጫና ነፃ በሆኑ ፓርቲዎች(አከላት) የሚተዳደሩ ከሆኑ፣ አካሄዱ የክልል መንግሥታት ሥልጣንን ያጠናክራል፡ ክልላዊ ጉዳዮች የማስተዳደር ችሎታቸውና የክልላቸውን ፍላጎት በፌደራል መንግሥቱ ደረጃ በትክክል እንዲወከል የማድረግ አቅማቸውን ያሳድጋል» (ሎቪስ አለን 2002: 78-9)

ኢህአዴግ ካለው የአስተዳደር አወቃቀር ጋር ጎን ለጎን የሚሄድ ከፌደራል ደረጃ ጀምሮ እስከ ጎጥ ድረስ የሚወርድ የፓርቲ መዋቅር አለው። አለን ይህንን ሁኔታ ሲያብራራ እንደሚቀጥለው ይላል «በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ሂወት ያለው አጠቃላይ ችግር የአስተዳደር መዋቅሩ ከፓርቲ መዋቅሩ ለመለየት ያለው ችግር ነው። ሰዎች ፓርቲውንና መንግሥቱን አንድ አድርገው ወደ ማየት ያዘነብላሉ። ይህ ችግር በፌደራል፡ በክልልና በታችኛው ደረጃም የሚታይ ነው። በከፍተኛ ደረጃ የማዕከላይ ኮሚቴው አመራር፡ የፓርቲው አስፈጻሚ አካላትና የመንግሥት የበላይ አስፈፃሚ አካላት ሁሉም በመሰረቱ አንድ ዓይነት ሰዎች ያቀፉ ስለሆኑ ለመለየት ያስቸግራል» (ሎቪስ አለን 2002: 80)

የገዢው ፓርቲ በክልሎች አስተዳደር ጠንካራ ጣልቃ ገብነት ያለው መሆኑ የፓርቲና የአስተዳደር አካላትን ለመለየት አስቸጋሪ መሆኑ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ጊዜም ፓርቲው ከክልሉ አስተዳደር አካላት ቅድሚያ የሚወስዱበት ሁኔታ መኖሩ ነው። ፍስሃና አየነው በትክክል እንዳስቀመጡት ሁሉ «የፌደራል መንግሥቱ እንዳለ ፣ መንግሥታቱ መገናኘት በሚገባቸው ሕጋዊ ወይንም እውቅና በተሰጣቸው የትብብር መስመር ሳይሆን በአብዛኛ ው የሚጠቀመው በፓርቲው ሕጋዊ ያልሆነ የተለምዶ  መስመር ነው (አሰፋ ፍስሃ 2006: 152) አብዛኛዎቹ የወረዳ አስተዳዳሪዎችና የወረዳው የምክር ቤት አባላት ደግሞ ሚናቸው ማዕከላይ መንግሥትና ፓርቲውን መወከል አድርገው ያምናሉ። ስለሆነም ከአካባቢው ሕ/ሰብ አሳሳቢ ጉዳዮችና ፍላጎቶች ይልቅ  የመንግሥትና የፓርቲ ትእዛዝ መሸከም ቅድሚያ ይሰጣሉ። በመጀመሪያ በወረዳ ደረጃ ያሉት አብዛኛዎቹ ሠራተኞች ሥራውን ያገኙት የገዢው ፓርቲ አባላት ወይንም ደጋፊዎች በመሆናቸው ስለሆነ ለፓርቲው ጉዳይ ቅድሚያ መስጠታቸው ሊገባን የሚችል ጉዳይ ነው» (ምህረት አየነው 2002: 144-5)

በፓርቲው አሰራር ከፍተኛ ፖለቲካዊ ውሳኔ ሰጪው አካል የፓርቲው ጉባኤ ሲሆን የቀን ተቀን ተግባሮችን ለመከታተል ይችል ዘንድ ደግሞ የተወሰነ ሥልጣን ለፓርቲው ማ/ኮሚቴ ያሰጣል፡፡ አለን(Aelen) በኦገስት **2000** ከገብረአብ ባርነባስ ጋር ባደረገው ቃለ-ምልልስ መሰረት የሚቀጥለውን ይላል፡፡ «በሥልጣን ያለው ግንባር (ገዢው ፓርቲ) የአራቱ የግንባሩ አባላት ከሆኑ ፓርቲዎች በሚወከሉ **60** አባላት ባካተተው ማ/ኮሚቴ ይመራል፡፡ ማ/ኮሚቴው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይመርጣል፡ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ከየአንዳንዱ አባል ድርጅት **5** ሰዎች የተወከለበት ነው፡፡ በጉባኤው መካከል ባለው ጊዜ ማ/ኮሚቴውና ሥራ አስፈፃሚው አካል የቀን ተቀን ሥራውን ይከታተላሉ፡፡ ጉባኤው በየሁለቱ ዓመቱ የሚካሄድ ነው፡፡ የፓርቲው ጉባኤ የኢህአዴግን አጠቃላይ ፕሮግራሞች ይወስናል፡፡ ሆኖም ማ/ኮሚቴው በአገር አቀፍ ደረጃ ተግባር ላይ የሚውሉ የኢህአዴግ የአምስት ዓመት ፕላንን መሰረት ያደረጉ ዝርዝር የተግባር ፕላኖች የማውጣትና ሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴን እንደ አካልና በግለሰብ ደረጃ የመምረጥና የማውረድ ሥልጣን አለው፡፡ (ሎቪስ አለን፡ 2006)

አራቱ የኢህአዴግ አባል ፓርቲዎች እናት ፓርቲው እንደሚያደርገው ሁሉ ከማ/ኮሚቴው ጋር ተመሳሳይነት ያለው ኮንሰልና ሥራ አስፈጻሚ በክልል በወረዳና ቀበሌ ደረጃ ያዋቅራል፡፡ የእነዚህ የፓርቲው አካላት ተጠያቂነት ከነሱ በላይ ላለው የፓርቲው አካል ሲሆን በመጨረሻም ከከፍተኛው የኢህአዴግ ማ/ኮሚቴ ጋር ይተሳሰራል፡፡ ትእዛዞች ከላይኛው ወደ ታችኛው የፓርቲ አካላት ይወርዳሉ፡፡ በተመሳሳይ ሰንሰለት ደግሞ መረጃ ከታች ወደ ላይ ይሄዳል፡፡ እንደ አለን አገላለጽ «በየአካባቢው ያሉት ከህዝቡ መረጃዎችን እየሰበሰቡ ለድርጅቱ የሚያስተላልፉ ካድሬዎች «ጆሮ» የሚል ስም በሰፊው መጠሪያቸው እየሆነ ነው፡፡ (በ**2000** እና በ**2001** ዓ.ም በትግራይና አ/አበባ ላይ በተደረገው ምርጫ ድምፅ ከሰጡት አካላት ጋር የተደረገው ቃለ-ምልልስ የተገኘ መረጃ)» (ሎቪስ አለን፡ 2002: 80) የታችኞቹ ፓርቲ አካላት በላይኞቹ ፓርቲ አካላት ትእዛዝ ሥር ስለሆኑ የላይኞቹ ፓርቲ አካላት ውሳኔ የታችኞቹ የፓርቲና የመንግሥት የምክር ቤት አካላት ከሚሰጡት ውሳኔ የበለጠ ሚዛን አለው፡፡

በአጠቃላይ የገዢው ፓርቲ በፌደራሉ መንግሥታዊ አካላት ላይ ያለው ልዕልና ክልላዊ ነጻነትን (Autonomy) እና በየደረጃው የተስተካከለ አሰራር እንዳይኖር እያደናቀፈ ነው፡፡ በ**2001** በህወሐት አመራር ውስጥ የተፈጠረው ክፍፍል ለዚህ ግልጽ ማስረጃ

ነው። በመሰረቱ የህወሐት ማ/ኮሚቴ ክፍፍል የክልል አስተዳደሮችን ዕለታዊ ሥራዎች መንካት አልነበረበትም፡ ይሁን እንጂ የፓርቲው ፖለቲካዊ ቀውስ ወደ መንግሥታዊው አካላት በቀጥታ ነበር የተላለፈው። በዚህ ምክንያትም በመንግሥታዊ አካላት ለብዙ ወራት የተፈጠረው አለመረጋጋት በመጨረሻ ላይ የተፈታው መንግሥታዊ አካላቱ በሕገ-መንግሥቱ መሰረት ያለመከሰስ መብት የነበራቸው የምክር ቤት አባላቶቻቸው በዘፈቀደ (arbitrarily) ከፓርቲውና ከመንግሥት ሥልጣናቸው እንዲያባሩ የሚለው የገዢ ፓርቲው ውሳኔ በመቀበል ወይንም በማክበር ነበር፡፡ ምክንያቱ «የፌደራል መንግሥታት ግንኙነት በኢትዮጵያ በፓርቲ ሥልጣን ላይ ለሚደረግ ለውጥ በጣም ቅርበት አለው»። የፓርቲው አመራር መከፋፈልና የተለየ ሐሳብ ያላቸውን የማባረር ተግባር «በደቡብ ህዝቦችና በኦሮሚያ ክልል ፓርቲ አባላት ላይም ትልቅ ጫና ነበረው» ( አሰፋ ፍሰሃ - **2006፡ 155)**። ባጭሩ «ይህ የፓርቲው አወቃቀርና አሰራር ውጤት የሆነው በሶቭየት ፌደራሊዝም መሠረት «ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት» ተብሎ የሚጠራው የሚያመለክተው በኢህአዴግ የሚጽድቁት ፖሊሲዎች ሁሉ የክልል መንግሥታትም ጥያቄ ውስጥ ሳያስገቡ መቀበል ወይንም መከተል እንዳለባቸው ነው።» (ደቪድ ቱርቶን **2006፡ 17)**

### 3.5 ሥርዓቱን ያገናዘበ ፋይናንሳዊ ፌደራሊዝም ያለመኖሩ

በፌደራልና ክልላዊ መንግሥታት መካከል የሥልጣን ክፍፍል ማድረግ የፌደራሊዝም አንድ አስፈላጊ ተግባር ቢሆንም የሃብትና የገንዘብ ክፍፍል ደግሞ በፌደራሊዝም ሂደት ቁልፍ ሚና አለው። የክልል መንግሥታት በሃብት ቁጥጥር ክፍፍልና አስተዳደር ላይ የተወሰነ ሚና እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። ለፋይናንሳዊ ነጻነት (Autonomy) በቂ ምኅዳር ወይንም ቦታ የማይሰጥ የፌደራል ሥርዓት ደግሞ እንደ እውነተኛ የፌደራል ሥርዓት ተደርጐ ሊታይ አይችልም።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የገቢና ወጪ አስተዳደር ሥርዓት ያጠኑ ተመራማሪዎች በአሁኑ ጊዜ የክልል መንግሥታት ባጀት በሚመለከት በትልቁ የፌደራል መንግሥት ጥገኛ እንደሆኑ ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል። አለን ክልሎች ባጀትን በተመለከተ በፌደራል ሥርዓቱ ላይ ጥገኛ መሆናቸው በሚመለከት እንዲህ ይላል፡ «ሕገ-መንግሥቱ የክልል መንግሥታት የራሳቸው ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችና ባጀት ማቀድና መተግበር እንደሚችሉ ይፈቅዳል። ግብርን ማስከፈልና ማስተዳደር፡ በሥልጣናቸው ሥር ያለው

ክፍያና ከአገር ውስጥ ምንጮች ብድር የመበደር ሥልጣንም አላቸው። ይሁን እንጂ በክልሎች ሥልጣን መዕቀፍ ሥር ያሉት የግብር ዘርፎች ብዙ ገቢ የሚያስገኙ አይደሉም። ከአገር ውስጥ ምንጮች መበደር የሚለውም ሂደቱ በጣም አስቸጋሪና በጣም አናሳ ከመሆኑ በላይ ተግባራዊ ጥቅም የሌለው ነው። የዚህ ውጤት ክልሎች በእጅጉ የፌደራል መንግሥት ድጐማ ጠባቂ መሆን ነው። ይህ ደግሞ ግልጽ የሆነ ወጥነት ያለው ኢ-ሚዛናዊነት ያመለክታል። ( ሎቨስ አለን 2002፡ 72) አየነውም የአለንን አባባል የሚቀጥለውን ሐሳብ በመጨመር ያጠናክረዋል። «በኢትዮጵያ ከላይ ወደ ታች የመውረድ ባህሪ ያለው ጉሳ ላይ የተመሠረተ ፌደራሊዝም ሌላው መገለጫ ደግሞ ክልሎች ባጀትን በተመለከተ በፌደራሉ መንግሥት እጅጉን ጥገኛ መሆናቸው ነው»

የኢትዮጵያ መንግሥት ዋነኛ የገንዘብ ምንጮች የጉምርክ ቀረጥ፣ የተጨማሪ እሴትና ከንግድ ድርጅቶች የሚገኝ የገቢ ግብር ( Customs tax, Value added and Corporate tax) ሲሆኑ ሁሉም በፌደራል መንግሥቱ ቁጥጥር ሥር ናቸው። በዚህ የክፍፍል ሥርዓት ለክልል መንግሥታት የሚተወው የመሬት ግብር፡ ከክልሉ የመንግሥት ሠራተኞች የሚሰበሰበው የገቢ ግብርና ውሱን የሮያሊቲ ግብር ነው። የክልሎች የግብር መሰረት ጠባብና ደካማ ስለሆነ ትላልቅ የሚባሉት እንደነ ኦሮሚያ፣ አማራና ደቡብ ህዝቦች የመሳሰሉ ክልሎች እንኳ ከየአካባቢያቸው በቂ ገቢ ለመሰብሰብና ዓመታዊ ባጀታቸውን ለመሸፈን የሚችሉበት ሁኔታ የለም።

ይህ የሚያመለክተው የክልል መንግሥታት ባጀታቸው ብቻ ሳይሆን ፡ ፖለቲካዊ ሥልጣኑም በሚቆጣጠረው የፌደራሉ መንግሥት ላይ እጅግ ከባድ የባጀት ጥገኝነት እንዳላቸው ነው። ክልሎቹ ሃብት የሚያሰባስቡበት በቂ አቅም ስሌላቸውና ባጀትን በሚመለከትም የፌደራል መንግሥትን ጥገኞች በመሆናቸው የተነሣ ከማእከላዊው መንግሥት ጋር በእኩልነት የሚደራደሩበት ሁኔታ ላይ አይደሉም። በኢትዮጵያ ፌደራል ሥርዓት በተጨባጭ እየታየ ላለው የሃብት ክፍፍል አለመመጣጠን ተመራማሪዎች የአጭር ጊዜ መፍትሄ ሊያስቀምጡለት አልቻሉም። ስብሩ እንደሚለው «ተነጻጻሪ የኢኮኖሚ እድገት በሌለባቸው አገሮች ውስጥ ሥር የሰደደ መዋቅራዊ ችግር በመኖሩ በናይጀሪያና በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የፋይናንስ መረን የለቀቀ ማዕከላዊነት መፈታት የሚችለው ዓመታት ወይንም አስር ዓመታት ባስቆጠረ ሰፊ መሰረት ባለውና ባልተማከለ የኢኮኖሚና የፖለቲካ እድገት ብቻ ነው። (ሮቲም ሰብሩ 2006፡ 87)»

ይህ እንዳለ ሆኖ የአሁኑ የኢትዮጵያ ፊሲካል ፌደራሊዝም በሚመለከት ግራ የሚያጋባው ነገር ቢኖር፡ የአሁኑ የፌደራል ወይንም ክልላዊ አስተዳደሮች ልክ በኃይለ

ሥላሴና በደርግ ጊዜ እንደነበሩት የበፊቶቹ ጠቅላይ ግዛቶችና ራስ ገዞች ደካሞች ሆነው መገኘታቸው ነው። ይህ የተዛባ ሁኔታ እስካልተስተካከለ ድረስ ደግሞ በኢትዮጵያ እውነተኛ ፌደራሊዝም ሊያብብ የሚችልበት ሁኔታ አይኖርም።

**3.6 የፌደራል ሥርዓቱ በተመለከተ የሚነሡ ሌሎች ችግሮች**

በኢትዮጵያ በብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሠረተ ፌደራሊዝም የመመሥረት ፍላጐት በኢህአዴግ ፖለቲካዊ ፕሮግራም ውስጥ ለረዥም ጊዜ የተንፀባረቀ ቢሆንም በፌደራል ሥርዓቱ ውስጥ ካሉት እስከ አሁን ተለይተው ከታዩት ችግሮች አንጻር ሲታይ ግን የኢትዮጵያ ፌደራሊዝም ቀያሽ የሆነው ኢህአዴግ፡ ወደዚህ ተግባር የገባው በፌደራሊዝም ላይ በቂ እውቀትና ተሞክሮ ሳይኖረው መሆኑ ነው። አየነው በዚህ ጉዳይ ላይ የሚቀጥለውን ይላል «ከሕግ አንጻር (formally) የክልል መንግሥታት ብዙ ጉዳዮችን ያጠቃለለ ሰፊ ሥልጣንና ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል፤ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችም ከፌደራል መንግሥት ጣልቃ ገብነት ነጻ በሆነ መንገድ ማስተዳደርም ይጠበቅባቸዋል። በተግባር ግን የአገሪቱ የፌደራል ሥርዓት የማስተዳደር ተሞክሮ ማነስና በክልሎቹ መኻከል ያለውን የማስተዳደርና የአመራር ብቃት ልዩነት ማዕከላዊ መንግሥት በክልሎች ጉዳይ ላይ ተደጋጋሚ ጣልቃ ገብነት እንዲያሳይ አድርጐታል።» (ምሕረት አየነው - 2002: 138-9)

በቋንቋ ላይ የተመሠረተ (እንደ ኦሮምኛ፣ አማርኛ፣ ትግርኛ፣ ሶማሊኛ፣ አፋርኛና ሐረሬ) የፌደራል ሥርዓት የመመስረት ተግባራዊ ችግሮች ከላይ ከተገለጹት ችግሮች ጋር የተሳሰሩ ናቸው። የተመሰረቱት የክልል አስተዳደሮች የህዝብ ብዛት ከ20 ሚልዮን እስከ 250,000 የሚለያይ እንደመሆኑ መጠን በክልሎች መካከል ትልቅ ልዩነት ፈጥሯል። ትላልቅ ክልሎች ትናንሽ ክልሎችን በሥራቸው የማስገባት አስፈላጊነት አስበውብታል ባይባልም ሳይሰማቸው ግን አይቀርም።

አደኒ (Adeney) የዚህ ዓይነት ችግሮች ሲገልጽ እንዲህ ይላል። «በክልሎች መካከል የህዝብ ብዛት ልዩነቱ ሰፊ ሲሆን የማዕከላይ መንግሥትን አሰራር ስለሚነካ የተለያዩ ትላልቅ ግጭቶችን ይፈጥራል። ይሁን እንጂ የየክልሉ የመሬት ስፋትና የሃብት ክፍፍልም በጣም አስፈላጊዎች (relevant) ናቸው። በክልላዊ አስተዳደሮቹ መካከል ያለውን የቆዳ ስፋት (Size) ልዩነትም ክልሎች በአካባቢያቸው ሊኖራቸው ከሚችለው ድምፅ የመስጠት ጥንካሬ አንፃር - ሲታይ ውጥረትን ሊያባብስ ስለሚችል በጣም አስፈላጊ መለያ ነው» Adeney 2000: 22

በእነዚህ ክልሎች መካከል ላለው ዓይነት ያለመመጣጠን በመጋለጥዋ ናይጄሪያ፡ የትላልቅ ክልሎች ትናንሾችን የመቆጣጠር ፍላጐት ለማቀዝቀዝ ወይንም ለማለዘብ አንድ ቋንቋ ይናገር የነበረው ትልቁ ክልል ወደ ትናንሽ ክልሎች (States) ከፋፍላለች፡፡ አንድ አንድ ትላልቅ የፌደሬሽኑ አባላት አሁንም ነጻነት እየጠየቁ ባሉበት፣ ሌሎቹ ደግሞ ብሄራዊ ማንነታቸውን ትተው ወደ ትናንሹ አስተዳደሮች እንዲከፋፈሉ ዝግጁ ባልሆኑበት የኢትዮጵያ ሁኔታ ይህ የናይጄሪያው ተሞክሮ እስከምን ድረስ ጠቃሚነት እንደሚኖረው እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡

የኢትዮጵያ የፌደራሊዝም ሥርዓት ሌላው ችግር በፌደራል መንግሥትና በብሄሮችና ብሄረሰቦች መብትና ሥልጣን መካከል ግልፅ ወሰን የሌለ መሆኑ ነው፡፡ በተለመዱ የፌደራል አወቃቀሮች የፌደራልና የክልል መንግሥታት ሥልጣኖች በሕገ-መንግሥት የተወሰኑና የተከፋፈሉ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሥርዓት ግን ወደ ፌደሬሽን ም/ቤት የመወከል ሥርዓት በክልላዊና ብሄር ብሄረሰባዊ መመዘኛዎች የተመሰረቱ ናቸው፡፡ የመገንጠል መብትም ለመንግሥታት ሳይሆን ለብሄር ብሄረሰቦዎቹ የተሰጠ መብት ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ሂደት የፌደሬሽኑ አባል መንግሥታትና ፌደራሊዝሙን ያልተረጋጋ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ብሄር ብሄረሰቦች ከፌደሬሽኑ የመገንጠል ምርጫ ሊወስዱ ወይንም ደግሞ የራሳቸውን መንግሥት ሊመሰርቱ በሚመርጡበት ሁኔታ የፌደራል ሥርዓቱና የክልል መንግሥታቱ መረጋጋት ለማስወገድ በማይቻልበት ሁኔታ ይነካል፡፡ የእንደዚህ ዓይነቱ አለመረጋጋት ግልፅ ምሳሌዎች በኢትዮጵያ በተጨባጭ እየታየ ነው፡፡ ለምሳሌ ሲዳማዎች የራሳቸውን ክልል ለመመስረት ጥያቄ ባቀረቡበት ጊዜ በፌደራል መንግሥት የአሉት መልስ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በሌሎች ብሄረሰቦች ለምሳሌ በስልጤዎች የቀረበው የራሳቸው አስተዳደር የመመስረት ጥያቄ ግን ግልፅ ባልሆነ ምክንያት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራሊዝም በፊቱ ነጻ ከነበሩ መንግሥታት ወይንም ክልሎች የተመሰረተ አይደለም፡፡ ከዚህ በፊት ጠቅላይ ግዛትና ራስ ገዝ አስተዳደር የነበሩትን በማሰባሰብ የተመሰረተ ነው፡፡ ከዘጠኙ ክልሎች የሰባቱ ማለትም የትግራይ፣ ሱማልያ፣ አፋር፣ ኦሮሚያ፣ ቤንሻንጉል፡ ጋምቤላና የአማራ ክልሎች አመሰራረት መነሻ በፀረ-ደርግ የትጥቅ ትግል ውስጥ ተሰማርተው የነበሩ መሆናቸው ይመስላል፡፡ እነዚህ ክልሎች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት በመጠየቅ የትጥቅ ትግል አካሂደዋል፡፡ ይህ ዓይነቱ የፌደራሊዝ አመሰራረት በሌላው ዓለም የተለመደ ባይሆንም በኢትዮጵያ ፀረ-ደርግ ትጥቅ ባነሱት የፖለቲካዊ ኃይሎች መካከል በመግባባትና ስምምነት ላይ የተመሰረተ የፌደራል ሥልጣን አወቃቀር ለመቅረፅ የተመረጠ አማራጭ ነበር፡፡ ይህ ዓይነቱ

የፌደራል አወቃቀር ግልፅ የሆኑ ችግሮች አሉት:: አንዱ ችግር አደናይ ከፍ ብሎ ከገለጸው ችግር ጋር የሚተሳሰር፣ በክልሎች መካከል ካለው የማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ እድገት ልዩነት ጋር የተሳሰረ ነው:: በኢትዮጵያ ሁኔታ ፌደራል ሥርዓቱን የመሰረቱት አካላት በሁለት ቡድን የተከፋፈሉ ናቸው:: የመጀመሪያው ቡድን «አራቱ ትላልቅ ክልሎች» (ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ ህዝቦችና ትግራይ) ሲሆኑ ሁለተኛው ቡድን ደግሞ «አራቱ በእድገት ላይ ያሉ» (ሶማልያ፣ አፋር፣ ቤኒሻንጉልና ጋምቤላ) ናቸው:: ሃረሬ የፌደራሉ ልዩ የከተማ መንግሥት ወይንም ክልል እንደመሆንዋ መጠን በሁለቱም ቡድን ሥር አትካተትም::

በክልሎች መካከል ያለው ግልጽ ልዩነት ምክንያት ለክልሎቹ ነጻነትና እድገት በሚል መጀመሪያ በጠቅላይ ሚኒስተር ጽ/ቤት ሥር የክልሎች ጉዳይ ጽ/ቤት፡ ከዛ በኋላ ደግሞ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር በማቋቋም፡ በፌደራል ሥርዓቱ ጠንካራ ክንድ ሥር እንዲሆኑ ለተደረጉት «በማደግ ላይ ለሚገኙት» ክልሎች ትልቅ ትርጉም ያለው ነው:: በከፊልም ቢሆን በዚህ ምክንያት «በማደግ ላይ» ያሉት ክልሎች ብዙ ጊዜ ለአመራር ቀውስና ለተደጋጋሚ የአመራር ለውጥ ተጋልጠዋል:: የፌደራሉ መንግሥት የአብዛኛ ዎቹ ክልሎች ውስጣዊ ጉዳይ በፓርቲው በተመደቡ ካድሬዎች እንዲመሩ በማድረግ አብዛኛዎቹን ክልሎች በፓርቲው መዋቅር ለመቆጣጠር ለረዥም ጊዜ ሞክሯል:: ነገር ግን በሂደት ወይንም ከጊዜ በኋላ እነዛ ካድሬዎች ተነስተው በጣም በተጠናከሩት የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር ባለሥልጣኖች እንዲተኩ ተደርገዋል:: ይህ ሁሉ የፌደራል አወቃቀር በሚባለው ሥርዓት ውስጥ፡ በጣም አስፈላጊ የሆነውን የክልሎቹ ውስጣዊ ነጻነት መርህ ያኮላሸ ነው::

ከላይ የተገለጸውን በመጻረር አንድ አንዶቹ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሥርዓት፡ በተለይ የመገንጠል መብትን ያካተተ በመሆኑ፡ ሰፊ ነፃነት ያጐናፀፈ ነው በማለት ይከራከራሉ:: ይሁን እንጂ በግልጽ እንደሚታየው ኢትዮጵያ የፌደራል ሥርዓቱን እንቅስቃሴ ውስጥ የገባችው፡ የተማከለ ጠንካራ መንግሥት፡ የመመስረት ጠንካራ ፍላጐት አስከትላ እንደሆነም ነው:: ለዚህ ሁሉ ማረጋገጫ በክልሎች ጉዳይ ላይ ያለምንም ገደብ በነጻነት ጣልቃ እንዲገባ ፈቃድ የተሰጠው የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትርን ያልተገደበ ሥልጣን መፈተሽ ብቻ ይበቃል::

በፌደራል መንግሥት ቁጥጥር ሥር ያለውን የፌደራል ፖሊስና በተወሰነ ደረጃም ቢሆን : የመከላከያ ሠራዊቱ በየክልሎቹ ያለውን የተጠናከረ ህልውና፡ የተማከለ ጠንካራ መንግሥት የመፍጠር ፍላጐት እያደገ መሆኑ የሚያሳይ ሌላ ምልክት ነው:: ይህ እንዳለ

ከቀጠለ ወይንም ማቆሚያ ካልተበጀለት ደግሞ ሊታይ ወይንም ሊኖር የሚችለው ውጤት ከአሁኑ የባሰ የኢትዮጵያ ፌደራሊዝም በወረቀት ላይ የሰፈረ ብቻ መሆኑ ነው።

## 4.ማጠቃለያ

የብሄር ብሄረሰቦች ማንነትና መብት የመረጋገጥ ጥያቄ በኢትዮጵያ ለብዙ አሰርት ዓመታታ አንገብጋቢ ጉዳይ ሆኖ ቆይቷል። በአገሪቱ ያሉ የተለያዩ ብሄሮችና ብሄረሰቦች ማንነታቸው እውቅና እንዲያገኝ ታግለዋል። በከፊልም ቢሆን ይህ የአሁኑ የአገሪቱ ፖለቲካዊ ሥርዓት አወቃቀር የዚህ ትግል ውጤት ነው። ሆኖም የፌደራል ሥርዓት ተዋቅሯል ቢባልም አሁንም አንዳንድ ብሄሮችና ብሄረሰቦች ማንነታችን በአግባቡ እውቅና አላገኘም በሚል በተለያዩ መንገዶች ትግል እያካሄዱ ይገኛሉ። የተወሰኑ የራሳቸውን መንግሥት ለመመስረት ይችሉ ዘንድ የመገንጠል መብት እንዲረጋገጥላቸው እየጠየቁ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ የይስሙላ ሳይሆን እውነተኛና ፍትሐዊ የሆነ በብሄር ብሄረ ሰብ መብት መርህ ላይ የተመሰረተ የፌደራል ሥርዓት ተግባራዊ እንዲሆን እየጠየቁ ነው።

አንዳንድ ተቺዎችና የፖለቲካ ቡድኖች በብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሰረተ ፌደራሊዝም የሊቨራል ዴሞክራሲ መርሆዎችን ይጻረራል ሲሉ አሁን በኢትዮጵያ እየተከሰተ ላለው ፖለቲካዊ ችግሮች መነሻ አድርገው ይወስዱትና ብሄር ብሄረሰብን መሠረት ያደረገ ፌደራሊዝም እስከነ አካቴው መሰረዝ አለበት ይላሉ። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ የብዙ ብሄር ብሄረሰቦችና ቡድኖች አገር በመሆንዋና የነዚህ የተለያዩ ህዝቦች ባህል፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መብቶች ዓለም ዓቀፍ እውቅና ባገኘበት ወቅት የብሄር ብሄረሰቦች ጥያቄን እንዲሁ መሰረዝና በጉሳ ላይ የተመሰረተ ፌደራሊዝም የግል መብትን የሚጻረር ጠላት ነው ብሎ መከራከር ካለው እውነታ የራቀ ይሆናል። እንዳውም በኢትዮጵያ ሁኔታ የግልና የቡድን መብቶች ተለያይተው የሚታዩበት ሁኔታ የለም። ስለሆነም ተነጣጥለው እንዲታዩ ማድረግ ለአገሪቱ የፖለቲካ ሂደት የሚጠቅም አይሆንም። በኢትዮጵያ የብሄር ብሄረሰቦች መብት ወይንም የወል መብት መከበር ለግለሰብ መብት መከበር የሚፈጥረው አደጋ አይኖርም። እንዲያውም የብሄር ብሄረሰቦችና የቡድን መብት እንደሌለ ተደርጎ ማለፉ የሊቨራል ዴሞክራሲ መርሆዎችን የሚፃረር ይሆናል። በተለይ የቡድን መብቶች መከበር ዓለም ዓቀፍ እውቅና አግኝተው በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር እንዲካተቱ በተደረገበት በአሁኑ ዘመን ይህን ሐሳብ

መሰንዘር ከፍተኛ መፋለስን ሊፈጥር ይችላል፡፡ አማራጩም እንዚህ እውቅናና መብት በመጠየቅ ላይ ያሉትን ብሄር ብሄረ ሰቦች በሃይል በመደፍጠጥ በአንድ ለማጠቃለል መሞከር ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ ፀረ ዴሞክረሲና ሠላምን የሚያውክ አካሄድን ያሰከትላል፡፡ ስለሆነም በኢትዮጵያ በብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሰረተ ፌደራሊዝም መከተልና መተግበር የህዝቦች ቋንቋ፣ ባህል፣ ማኅበራዊ፡ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መብቶች ከማስከበር አንፃር ትክክለኛ አቅጣጫ ይሆናል፡፡ አንድነትንና ልዩነትን አጣጥሞ መሄድ ተመራጩ አካሄድ ይሆናል፡፡

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሥርዓት ሌላው አከራካሪ ጉዳይ 1994 ዓ.ም በፀደቀው ሕገ-መንግስት የብሄር ብሄረሰቦች እስከ መገንጠል መብት መካተቱ ነው፡፡ እውነቱን ለመናገር ይህ ጉዳይ በብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሰረተ ፌደራሊዝም አይጠቅምም ከሚለው ሐሳብ በላይ የሚያለያይና የሚያከራክር ነው፡፡ ብዙ የፖለቲካ ቡድኖች የአገሪቱን አንድነት አደጋ ላይ የሚጥል አርገው ይወስዱታል፡፡ የመገንጠል መብት በሕገ-መንግሥቱ መካተቱ የሚቃወሙ ኃይሎች ይህ አንቀፅ አገሪቱን የሚበታትን ተጨባጭ አደጋ ነው ይሉታል፡፡ በመሆኑም ከሕገ-መንግስቱ መፋቅ ያለበት አንቀፅ ነው ይላሉ፡፡ ሆኖም የዚህ አንቀፅ ከሕገ መንግሥቱ መፋቅ ብቻውን በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የተደቀነውን አደጋ የሚያስወግድ ወይንም የሚፈታ አይሆንም፡፡ የመገንጠል መብት በሕገ-መንግሥቱ የተካተተበት አንዱ ምክንያት የመገንጠል መብትን በፕሮግራማቸው ውስጥ በመካተት ሲታገሉ የነበሩን ቡዱኖችና አካባቢዎች ለማቀፍ ተብሎ ነው፡፡ ይህ አንቀጽ በሕገ መንግሥት ከመደንገጉ በፊት በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶች የመገንጠል ጥያቄ በፕሮግራማቸው አስፈረው ነበር፡፡ ህወሓት፣ አነግ የሶማልያ ድርጅቶች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እነዚህ ቡድኖች የመገንጠል መብት በሕገ-መንግሥት መካተት ብሄራዊ ጭቆና ዳግም እንዳያገረሽ በዋስትናነት የሚመለከቱትና እንደ መከላከያ መሣርያ የሚያዩት ነው፡፡ ስለሆነም የመገንጠል መብት ከሕገ መንግሥቱ መፋቅ በአገራችን ሁኔታ ሊያስከትል የሚችለውን ቅሬታና ችግር በአግባቡ ግምት ውስጥ በማስገባትና ሊፈጥረው የሚችለውን ቀውስና ያለመረጋጋት ታሳቢ በማድረግ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ጉዳዩ እጅግ አሳሳቢና አወዛጋቢ በመሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃና ግልፅ በሆነ አግባብ ተወያይቶበት መቋጫ ሊያበጅለት ይገባል፡፡

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ፖለቲካ መሰረታዊ ችግር በብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሰረተ ፌደራሊዝምን በመከተል ወይንም ለመገንጠል መብት እውቅና መስጠት

ያስከተለው ችግር አይደለም። እነዚህ ጉዳዮች ህዝቡ ለወደፊቱ ቀጣይ ውይይቶችና ክርክሮች በማካሄድ አስፈላጊ ሲሆንም ህዝበ ውሳኔ ወይንም ሬፈረንደም ሊያደርግባቸው የሚችሉ ጉዳዮች ናቸው። በጣም አሳሳቢው ችግር አሁን ባለው አገራዊ ሁኔታ የጋራ መግባባት ያለመኖሩና መሰረታዊ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች ጠፍተው የሚፈለገው ዴሞክራሲያዊ ሂደትና ግንባታ አደጋ ላይ መውደቁ ነው። እነዚህ ጉዳዩች አሃዳዊ ሥርዓት የሚፈልጉትንና እውነተኛ በብሄር ብሄረ ስብ ላይ የተመሰረተ ፌደራሊዝም የሚሹትን ወገኖች  የሚያሳስቡ አንገብጋቢ ጉዳዮች ናቸው።

የሥልጣንና የሃብት ክፍፍል ግልፅነት የመኖር ጥያቄ በፌደራሊዝም ወሳኝ ወይንም አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ትክክለኛ የሆነ የሥልጣን ክፍፍል ሥርዓት ዘርግቻለሁ፣ ብሎ ቢከራከርም፣ ተጨባጭ ሐቁ ግን ሕገ-መንግሥቱ የሚፈቅደውን የሥልጣን ክፍፍል ሥርዓት ባልተከተለው ኢህአዴግ ሥር ይበልጥ እየተማከለና በተወሰኑ ቡደኖች እጅ እየተጠቃለለ ነው። ከክልል ጀምሮ እስከ ወረዳና ጐጥ የሚደርስ የፓርቲው ህልውና ክልሎች በነጻነትና ያለ ጣልቃ ገብነት ሥልጣናቸውን ተግባር ላይ የማዋል ችሎታ እያዳከመ ነው። በተጨማሪ የፌደራል ሥርዓቱ በሃገሪቱ ሃብት ላይ ያለው ጠንካራ ክንድም የክልል መስተዳድሮችን ወይንም መንግሥታትን ወደ ተራ ክፍለ ሀገርነት ደረጃ አውርደዋቸዋል። አሁን ያለው ሥርዓት ፌደራሊዝም የጋራና የራስ አስተዳደር ነው የሚለውን መርህ በእጅጉ የሚጻረር ነው። በሥልጣንና ሃብት ክፍፍል ረገድ የጋራም ይሁን የራስ አስተዳደር አይታይም።

በኢትዮጵያ የፌደራል ሥርዓት ሂደት ሌሎች በግልፅ የሚታዩ ችግሮችም አሉ። በሕገ-መንግሥት ክልል የሚነሱ ልዩነቶች የሚያይ ነጻነቱ የተጠበቀ የሕገ-መንግሥት ፍርድ ቤት ያለመኖሩ፣ የተሟላ ሥልጣን ያለው የፌደሬሽን ም/ቤት ያለመኖሩ፣ የፌደራል መንግሥት በክልሎች ጉዳይ ላይ ጣልቃ መግባቱ በክልሎች የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስተር ግዙፍ ጣልቃ ገብነት ወዘተ. መፍትሄ ያላገኙ ጉዳዮች ናቸው። እነዚህ ሁሉ በመጀመሪያ የፌደራል ሥርዓቱ አቀራረፅ ላይ የተሳተፋ አንዳንድ ድርጅቶች ላይ ሳይቀር ትልቅ ቅሬታና ጥላቻ ፈጥረዋል። አንዳንዶቹም በተጠቀሱት ችግሮች ምክንያት የተነሣ የኢህአዴግን መንግሥት ለመዋጋት ትጥቅ አንስተዋል።

## ዋቢ የተደረጉ ጽሑፎች


Aalen, Lovise. 2002. Ethnic Federalism in a Dominant Party State: The Ethiopian Experience 1991-2000.

Adeney Kathrine. 2000. Regional Identity and Reconcilation: Federalism in India and Pakistan,

Bahru Zewde. 2002. History of Modern Ethiopia, 1885-1991.

ኢህአዴግ 2006 1999 ልማት፣ ዴሞክራሲና አብዮታዊ ዴሞክራሲ

ኢፌዴሪ 1995 /1987ዓ.ም/ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ሕገ መንግሥት

ኅዳር 1994 /1987ዓ.ም/

Mafeje,Archie. 1995. Multi Party Democracy and Ethnic Divisions in African Society; Are They Compatible?

Meherat Ayenew. 2002. 'Decentralization in Ethiopia: Two Case Studies on Devolution of Power and Responsibilities to Local Authorities.' In Bahru Zewde and Siegfried.

Messay Kebede.2006. The Ethnicizatin of Ethiopian Politics: Origins and Significance. Posted on Website.

Turton,David(ed.) 2006. Ethnic Federalism: The Ethiopian Experience in Comparative Perspective. References in Turton.

a)Will Kymlicka. 2006. Emerging Westen Models of Multination Federalism: Are They Relevant for Africa?

b) Rotimi Suberu.2006. Federalism and the Management of Ethnic Conflict: The Nigerian Exprience .

c) Merera Gudina.2006. Contradictory Interpretation of Ethiopian History: The Need for a New Consensus.

d) Rajeev Bhargava. The Evolution and the Distinctiveness of India's Linguistic Federalism.

e) Assefa Fisseha. Theory Versus Pracice in the Implementation of Ethiopia's Ethnic Federalism.

ዘውዱ ውብ እንግዳ /ዶክተር/፡ የፌደራል መንግሥት ታሪካዊ ዕድገትና የመንግሥት አወቃቀር ችግሮች በኢትዮጵያ እ.ኤ.አ 2005